# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 130 ጥር 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ኢትዮጵያ ለጀመረችው ለውጥ

## የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን አሻራ ትልቅ ቦታ ይኖረዋል



ፎቶ፡ ገበዘ ገብሬ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለጀመረችውና ወደ ኋላ ለማይመለሰው ለውጥ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን አሻራ ትልቅ ቦታ እንዳለው ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡

የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ይፋዊ የእንኳን ደህና መጣችሁ መርሀ ግብር ትናንት በወዳጅነት አደባባይ ተካሂዷል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጥሪን ተከትሎ ከተለያዩ ሀገራት ወደ ሀገር ቤት ለመጡ በውጭ የሚኖሩ ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ይፋዊ የእንኳን ደህና መጣችሁ መርሀ ግብር በወዳጅነት አደባባይ የተካሄደ ሲሆን፤ በመርሀ ግብሩ ላይ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ሀገራዊ ጥሪውን ተከትሎ በመጀመሪያው ዙር ከተለያዩ ሀገራት ወደ ሀገር ለመጡ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት አስተላልፈዋል።

"ጥሪውን አክብራችሁ በመጀመሪያ ዙር የመጣችሁ ስለ ሀገራችሁ ከምትሰሙት በላይ ተጨባጭ እውቀት የምታገኙበትን ቆይታ ታሳልፋላችሁ" ብለዋል።

ማህበራዊ ሚዲያውን ጨምሮ ወደ ሀገር ቤት እንዳትሄዱ የሚከለክሉ መልካም ያልሆኑ ሀሰተኛ መረጃዎችን አሸንፋችሁ በመምጣታችሁ ጀግኖች ናችሁ ሲሉ አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ወደ ኋላ መመለስ የማይችል ለውጥ ውስጥ ገብታለች

ኢትዮጵያ ለጀመረችው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## የክልሉን ሰላም

### ከማስጠበቅ ጎን ለጎን ፕሮጀክቶችን በወቀቱ ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው

### - በክልሉ የጥምቀት በዓልን ለማክበርም ዝግጅት ተደርጓል

ገጽ 2



አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን

## ስምምነቱ የኢኮኖሚ

### ተጠቃሚነትን ማሳደግ እንጂ ማንንም የመጉዳት ዓላማ የለውም

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ከሶማሊላንድ ጋር የተደረገው የመግባቢያ ስምምነት እያደገ ለመጣው የሕዝብ ቁጥርና የኢኮኖሚ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት እንጂ ማንንም አካል የመጉዳት ዓላማ እንደሌለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደኅንነት አማካሪ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገለጹ፡፡

በኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የውጭ ግንኙነትና ወታደራዊ ትብብር ዋና ዳይሬክቶሬት አዘጋጅነት

ስምምነቱ የኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ...

**ሄለን ወንድምነው እና ሔርሞን ፍቃዱ**



**ዜና ሐተታ**

የጥምቀት በዓል ሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ባህላዊና ማህበራዊ መስተጋብርም ይከወንበታል። በዓሉ በርካታ ሰዎች በሀገር ባህል ልብስ ደምቀው የሚታዩበትና የዕደ-ጥበብና ኪነ-ጥበብ ውጤቶች በስፋት የሚደመጡበት ነው።

ታዲያ ወይዛዝርቱ ለጥምቀት በዓል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተውበውና ደምቀው በዓሉን ለማክበር የመጀመሪያው እቅዳቸው ልባቸው የከጀለውን የባህል ቀሚስ መርጠው መዋብና መልበስ ነው። ለዚህም ነው ‹‹ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ››ተብሎ የተተረተው።

ጥምቀት ከሃይማኖታዊ እሴቱ በተጨማሪ ባህልና ወግን ማሳደጊያ፣ መተጫጫ፣ የሥነ-ልቦና ማደሻ፣ በመንፈስና በአካል ጎልቶ የመታያና የማንነት መገለጫ እንዲሁም ማህበራዊ መስተጋብር ጎልቶ የሚወጣበት ባህል ነው ያሉት በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ዳይሬክተር መስፍን ፈቃዴ (ዶ/ር) ናቸው።

ጥምቀት የተነፋፈቀ ዘመድ የሚገናኝበት፣ ወጣቶች የትዳር አጋራቸውን የሚመርጡበት በዓል ነው። በዚህም ሰዎች በበዓሉ አዲስ ለብሰው፣ አጊጠውና

ለጥምቀት ያልሆነ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# የክልሉን ሰላም ከማስጠበቅ ጎን ለጎን ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው

**- በክልሉ የጥምቀት በዓልን ለማክበርም ዝግጅት ተደርጓል**

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የክልሉን ሰላም ከማስጠበቅ ጎን ለጎን የተቋረጡ አገልግሎቶችን የማስጀመርና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ለማስቻል እየተሠራ መሆኑን የአማራ ክልል መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ በሚገኙ ሁሉም አካባቢዎች የጥምቀት በዓልን ለማክበር ዝግጅት መደረጉም ተመላክቷል።

የቢሮው ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የነበረውን የጸጥታ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በተሰራው የተቀናጀ ሥራ አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል።

የክልሉን ሰላም ከማስከበር ጎን ለጎን ተቋርጠው የነበሩ አገልግሎቶች እንዲጀምሩ የማድረግ፣ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ የማጠናቀቅና አዳዲስ የመሰረተ ልማትና ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተከናወነ መሆኑን አመላክተዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች ተቋርጠው የነበሩ የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶችን ማስጀመር እንደተቻለ ጠቁመው፤ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎቻቸውን እየተቀበሉ መሆኑን አስረድተዋል።

ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲገቡ የአካባቢው ማህበረሰብ አቀባበል እያደረገላቸው እንደሚገኝና በመንገድ ላይ ችግር እንዳይገጥማቸው የጸጥታ ኃይሉ ጥበቃና ክትትል እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ፀረ-ሰላም ኃይሎች እኔ ትምህርት አቋርጬ ሌላው ለምን ይማራል በሚል ተማሪዎች ትምህርት እንዳይማሩ የሚያደርጉትን ሙከራ ለማክሸፍ የአካባቢው የጸጥታ ኃይል በተጠናከረ ሁኔታ እየሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

ሰላም ከማስከበርና የተቋረጡ አገልግሎቶችን ከማስጀመር በተጨማሪም የተለያዩ የልማት ስራዎች በሁሉም አካባቢዎች እየተሰራ ነው ብለዋል።

የተጀመሩትን ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ የማጠናቀቅ፣ የአስፓልት መንገድ፣ የኮብልስቶንና የተለያዩ የመሰረተ ልማት ስራዎችን የማከናወን ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸዋል።

ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ አመራሩ ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ቁጥጥር እያደረገ መሆኑንም አስረድተው፤ በሚሰሩ ፕሮጀክቶችም ለዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል እየተፈጠረላቸው መሆኑን አመላክተዋል።

አልፎ አልፎ በአንዳንድ አካባቢዎች በግልና በቡድን በመሆን መንገድን የመዝጋትና የተለያዩ ግጭቶችን የሚፈጥሩ አካላት መኖራቸውን ጠቁመው፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በአመራር ደረጃ የሚገኙ የጸጥታ ኃይሎች በክልሉ በሚገኙ አራት ማዕከሎች ግምገማዊ ስልጠና እያካሄደ መሆኑን አስታውቀዋል።

ስልጠናው ከተጀመረ ከአንድ ሳምንት በላይ እንደሆነው ገልጸው፤ ስልጠናውን አጠናቀው ሲወጡ በየአካባቢያቸው ያለውን የጸጥታ ችግር በዝርዝር በመገምገም ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እንደሚሰሩ እና የጸጥታ አካላቱን በአመለካከትና በትጥቅ የማብቃት ሥራ እንደሚሰሩ ጠቁመዋል።

ፖሊሶች፣ ሚሊሻዎችና ሌሎች የጸጥታ ኃይሎች የአካባቢያቸውን ሰላም ለማስጠበቅ ከፌዴራል የጸጥታ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰሩ ይገኛሉ ሲሉም ገልጸዋል።

የጸጥታ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በተሰራው የተቀናጀ ሥራ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል ያሉት ኃላፊው፤ በዚህም ህብረተሰቡ ወደቀድሞው የሥራ እንቅስቃሴው ተመልሷል ሲሉ ተናግረዋል።

በተሰራው የቅንጅት ሥራ የገናን በዓል በላሊበላ ከተማ በድምቀት ማክበር መቻሉን አስታውሰው፤ የጥምቀት በዓልንም በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ ለማክበር ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

በዓሉ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር ለማድረግ የጸጥታ ኃይሉ ከምንጊዜውም በላይ ቁርጠኛ ሆኖ እየሰራ ነው ብለዋል።

ጥምቀት በልዩ ሁኔታ ከሚከበርባቸው አካባቢዎች አንዱ ጎንደር ከተማ መሆኑን ገልጸው፤ በዓሉን በሰላም ለማክበር የሃይማኖት አባቶች፣ የጸጥታ ኃይሉና ወጣቶች በቅንጅት እየሰሩ መሆኑን አመላክተዋል።

# ለበዓሉ መሰናዶ - በፍቅር የተገመደ አብሮነት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ሐተታ**

ከዓመት እስከ ዓመት ትዝታው በብዙዎች ዘንድ የሚደበዝዝ አይደለም፡፡ ብዙዎች የፍቅርና የመተሳሰብ ጽዋ በአንድነት ይጎነጩበታል፡፡ ጥቂት ለማይባሉ ሰዎች የመተባበርና የመረዳዳትን ውጥን መከወኛ ነው፤የጥምቀት በዓል፡፡



ጥምቀት ጉርብትናንና መረዳዳትን በማጽናት ረገድ የበዓላት ንጉስ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ከሃይማኖቱ ተከታዮች ውጪ ጥምቀትን የሚናፍቁ ብዙ ናቸው፡፡ ሁሉም አሻራውን ለበዓሉ ለማኖር ጎንበስ ቀና ማለቱ የተለመደ ነው፡፡

ባህረ ጥምቀት በህብረት ከማጽዳት ጀምሮ ታቦታቱ ወጥተው እስኪገቡ በእልልታና በሆታ በማጀብ የሚተጉ አያሌ ናቸው፡፡ በዕለቱም ምንጣፉን የሚሸከሙ፣ እየተሽቀዳደሙ ታቦት የሚያልፍበትን ቦታ የሚያጸዱ ወጣቶች፣ በየመንገዱ እየቆሙ ውሃ የሚያቀብሉ ሰዎች የትብብር መንፈስ ማሳያዎች ናቸው።

ለዓመት የናፈቋትን የጥምቀት በዓል መባቻ ቀን የማለዳው ጮራ ሰዓቷን ጠብቃ ብቅ ለማለት ስትዘጋጅ እንቅልፍና የሚጋረፍ ብርድ ሳይገታቸው ባህረ ጥምቀቱን ለማጽዳት የሻቱ እጆች ሥራ ጀመሩ።

በስፍራው በርካታ የተለያዩ የሃይማኖት አባቶች ተገኝተዋል፡፡ የሃይማኖት አባቶችን ቆራጥነት ላየ ባህረ ጥምቀትን ማጽዳት ለወጣቶች ብቻ ማን ሰጠው ብሎ እንዲያልፍ ይገደዳል፡፡

ባህረ ጥምቀት ለማጽዳት የመጡት የሃይማኖት አባቶች በርካታ ቢሆኑም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን ከሰጡት መካከል የሆኑት በወሎ ሰፈር ጥምቀተ ባህር ሲያጸዱ ያገኘናቸው የቅድስት ማርያምና ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ አባ ገብረመድህን ተሾመ አንዱ ናቸው፡፡

በዓለ ጥምቀቱ ፍቅርና አንድነት የሚገለጽበት በመሆኑ ከዋዜማው ጀምሮ የተለያዩ እምነት ተቋማት በጋራ እያጸዱ በመሆኑ እንዳስደሰታቸው አባ ገብረመድህን ያብራራሉ፡፡

ጥምቀት ማህበራዊ መስተጋብር ለማጠናከርና የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማዳበር አይተኬ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የሰው ልጆች የዕዳ ደብዳቤ የተሰረዘበትና ሰውና መላዕክት ዳግም በአንድነት የዘመሩበት በዓል እንደመሆኑ መጠን በሰላምና በፍቅር መከበር እንዳለበት ነው የሚያስረዱት።

የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑት አደም አብደላ በበኩላቸው፤ ለጥምቀትና ከተራ በዓል በተደረገው የጽዳት ዘመቻ በመሳተፋቸው መደሰታቸውን ተናግረው፤ በዓሉ በተለያዩ ሃይማኖቶች ዘንድ በመረዳዳትና በመተሳሰብ መከበሩ ትልቅ ሀገራዊ ፋይዳ አለው ይላሉ፡፡

በዓሉ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት የተመዘገበ በመሆኑ ይበልጥ ለማስተዋወቅና የሀገሪቱ መገለጫ ለማድረግ ሁሉም ሊተባበር ይገባል ባይ ናቸው፡፡

በዓሉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ምንም ዓይነት የጸጥታ ችግር እንዳይፈጠር የሁሉም ኃላፊነት ነው የሚሉት አደም፤ የኢትዮጵያዊያን የመተጋገዝና የመረዳዳት ባህል ለዓለም ተምሳሌት በመሆኑ በመጪው የጥምቀት በዓል መደገም እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

የአንዱ ሃይማኖት ዓመታዊ በዓላት ሲከበር ሁሉም በመተጋገዝ የሚፈጽመው በጎ ተግባር መልካም ተጽዕኖ መፍጠር የሚቻልበት አጋጣሚ ነው ያሉት ደግሞ ከኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያን ህብረት የመጡት ፓስተር ሙላቱ ኤርሚያስ ናቸው፡፡

የበዓሉ ባለቤት በዋናነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብትሆንም የሁሉም የጋራ ሀብት ነው የሚሉት ፓስተር ሙላቱ፤ ከበዓሉ የሚገኘው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሃሴት በተጨማሪ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተው ድርሻ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ብለዋል፡፡

እኛም በጽዳትና በተለያዩ ጉዳዮች በመተባበር አንድነታችንን ለማሳየት የፈለግነው በዓሉ የሰላም ምልክት በመሆኑ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

በጥምቀት በዓል ስለሰላምና ስለአንድነት በመስበክ ሁሉም የሃይማኖት አባት በአንድነት መቆም እንዳለበት በጽዳቱ የተሳተፉ የተለያዩ ዕምነት ተከታዮች መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



# በመዲናዋ የጥምቀት በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ ወጣቱ ለሰላም ዘብ መቆም አለበት

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮው የከተራና ጥምቀት በዓል በሰላም እንዲጠናቀቁ ወጣቱ ለሰላም ዘብ ሊቆም እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ "የከተራና የጥምቀት በዓል በሰላም እንዲከበር የወጣቶች ሚና" በሚል ሃሳብ ያዘጋጁት የውይይት መድረክ ትናንትና ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ፍቅሬ ግዛው እንደተናገሩት፤ የጥምቀት በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ ወጣቱ ከፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት ለሰላም ዘብ ሊቆም ይገባል።

በሰላም ጉዳይ የመጀመሪያ ተጋላጭ የሚሆነው ወጣቱ ነው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ ወጣቶች በመነጋገርና በውይይት መንፈስ በመስራት በዓሉን በሰላም ለማክበር የሚደረገውን እንቅስቃሴ ሊደግፉ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ ፍቅሬ እንዳመለከቱት፤ በመዲናዋ የጥምቀት በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ ከሃይማኖት አባቶች፤ በዓሉን ከሚያደምቁ ወጣቶችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ወይይት ተካሂዷል።

ወጣቶች እንደየክፍለ ከተማቸው ሁኔታ በሚያስፈልጉ ጉዳዮች ለበዓሉ በሰላም መከበር የራሳቸውን ሚና እንዲወጡ እና ከአጎራባች ክፍለ ከተሞችና አካባቢዎች ጋር እንዲሰሩ ለማስቻል የሚረዳ ውይይት መካሄዱን አመላክተዋል።

በመሆኑም ጥምቀትን ፣ በቀጣይ የሚካሄደውን የአፍሪካ ህብረት ስብሰባና የዓድዋ ክብረ በዓል በሰላም ለማክበር የሀገር ግንባታ በሚል የወጣቶች የንቅናቄ መድረክ ተጀምሮ በክፍለ ከተማና ወረዳዎች ከወጣቶች ጋር ወይይት ሲካሄድ ቆይቷል ሲሉ አስረድተዋል።

በሁሉም ዘርፎች የወጣቱ ተሳትፎ ከፍተኛ እንደመሆኑ በዓሉ በሚከበርበት ወቅት ችግሮች እንዳያጋጥሙ በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመስራት ከፍ ሲልም ችግር ሲገኝ ለጸጥታ አካላት አሳልፎ በመስጠትና እና በአካባቢው የሚመጡ እንግዶችን በሰላማዊ መንገድ ለመቀበል የሚረዳ ገንቢ ውይይት ሲካሄድ መቆየቱን አስታውሰዋል።

እንደምክትል ኃላፊው ገለጻ፤ የጥምቀት በዓል በዩኔስኮ የተመዘገበ ቅርስ እንደመሆኑ በርካታ ጎብኚዎች ይሳተፋሉ። ቢሮው በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ለማስቻል ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በዓሉ የሚከበርባቸውን አካባቢዎች የማጽዳት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል።

የጸጥታ አካላት በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ምን አይነት ስራዎች መስራት እንደሚጠበቅባቸው የውይይት መድረክ ተዘጋጅቶ ማብራሪያ ተሰጥቷል ሲሉ አስረድተዋል።

# "ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የመረጋጋት መንስኤ ናት"

- አምባሳደር መለስ አለም (ዶ/ር) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ

**ሞገስ ጸጋዬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የመረጋጋት መንስኤ ናት ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም (ዶ/ር) አስታወቁ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በትናንትናው ዕለት በዲፕሎማሲ ሳምንትና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያና ሶማሌላንድ የተፈራረሙት የመግባቢያ ስምምነት ሌሎች ሀገራት ካደረጉት የተለየ ባለመሆኑ ለኢትዮጵያ ሲሆን የተለየ ሊሆን አይችልም።

ግብጽን ጨምሮ ሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች አፍንጫችን ስር የባህር መዳረሻና ወደብ ሲከፍቱ ኢትዮጵያ ስታረገው ነውር የሚሆንበት አመክንዮ አይኖርም። ለኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ የፍትህ፣ የልማትና የሰላም ጉዳይ ስለሆነ የባህር መዳረሻ ያስፈልጋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ ከሰሞኑ በበይነ መረብ አማካኝነት በተካሄደው የአረብ ሊግ ጉባኤ ላይ የግብጽ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካ አለመረጋጋት ምንጭ ናት እንደሚለው ሳይሆን የመረጋጋት መንስኤ ናት። አረብ ሊግ ቀደም ሲልም ከአባይ ባህር ጋር በተያያዘ በርካታ መግለጫ ሲያወጣ መቆየቱን አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያ በሶማሌ የሰላም አስከባሪ ያሰማራችው ቀጠናው የተረጋጋ እንዲሆን ካላት ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ነው ያሉት አምባሳደር መለስ፤ እንዲሁም ለደቡብ ሱዳን ሰላምና ነጻነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላት። የሰው ዋጋ ተከፍሎበታል ብለዋል።



ኢትዮጵያ ለሱዳን በተከታታይ እስካሁን ድረስ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ነው ያሉት አምባሳደር መለስ፤ በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያን ለቀጠናው ያለመረጋጋት መንስኤ አድርጎ መክሰስ ቧልት ነው። በኢትዮጵያ በኩል በአካባቢው ሰላምና ልማት እንዲመጣ አበክራ ትሰራለች። ሁሉም ነገር በሰላም እንዲፈታ ትፈልጋለች። እየሰራችም ትገኛለች። 120 ሚሊዮን ሕዝብ አንቆ የሚያስቀምጥ የልማት ሁኔታ መለወጥ አለበት ብለዋል።

አረብ ሊግ በኢትዮጵያ ጉዳይ የሰጠው መግለጫ ተቀባይነት የለውም ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ይህ ድርጅት በአንድ ሀገር የሚዘወር ነው። የወጣው መግለጫ ተቋሙንና አባል ሀገራቱን የሚመጥን አይደለም። ከምንም በላይ ለአፍሪካውያን ንቀት ነው። አፍሪካውያን የራሳቸውን ችግር በራሳቸው የመፍታት ብቃቱ አላቸው፤ ይህንንም በተግባር አሳይተዋል ብለዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ በግብጽና በአረብ ሊግ መካከል ያለው ግንኙነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ተደርጎ መወሰድ አለበት። የግብጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሰጡት መግለጫ ኢትዮጵያና ግብጽ ካላቸው ግንኙነት አንጻር የሚመጥን አይደለም።

የኢትዮጵያና የሶማሌያን የንግድና የበረራ ግንኙነት በተመለከተ የተለወጠ ነገር የለም ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ከበረራ ጋር በተያያዘ አጋጥሞ የነበረው ጉዳይ ተፈቷል። አዲስ አበባና ሞቃዲሾ፤ አዲስ አበባና ሀርጌሳ መገናኘታቸውን ይቀጥላሉ። በሁለቱ ሀገራት የዲፕሎማሲ ግንኙነት መካከል የተለወጠ ነገር የለም ሲሉም አረጋግጠዋል።

አምባሳደር መለስ እንዳሉት፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሳይንስ ሙዚየም እየተካሄደ ያለው የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲው እንቅስቃሴ በተገቢው ማስተዋወቅ ችሏል። የኢትዮጵያን የረጅም ጊዜ የዲፕሎማሲ ታሪክ በማሳየት በአፍሪካ፣ የአፍሪካ ቀንድና በዓለም አቀፍ መድረኮች የተጫወተቻቸውን ሚና ለዜጎችና ለዲፕሎማሲ ማህበረሰብ ማሳየት ተችሏል። እንዲሁም ኅብረተሰቡ በቀጣይ እኔም ለሀገሬ አምባሳደር ነኝ በማለት ቃል እየገባ ነው። ለቀጣይ የዲፕሎማሲ ሥራ ትልቅ ጉልበት የሚሆን የኅብረተሰብ ድጋፍ የተገኘበት ነው።

በዓመታዊ የሚሲዮን መሪዎች ስብሰባ፣ በዳቮሱ የዓለም የኢኮኖሚ ፎረምና በገለልተኛ ንቅናቄ አባል ሀገራት ጉባዔ ኢትዮጵያ እየተሳተፈች መሆኑንም ቃል አቀባዩ ገልጸዋል።



## "የጥምቀት በዓል ከሃይማኖታዊ እሴቶቹ ባሻገር ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር ይረዳል"

- ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ፀሐፊ

**አማን ረሺድ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የጥምቀት በዓል ከሃይማኖታዊ እሴቶቹ ባሻገር ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር፣ የብሔር ብሔረሰቦችን ባህልና እሴት ለማዳበር እንደሚረዳ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ ገለጹ።

ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጥምቀት በዓል የኢትዮጵያን ምንነት ለተቀረው ዓለም ለማስተዋወቅ ዕድል የሚፈጥርና ህብረ ብሔራዊነትን ለማጠናከር የሚያግዝ ነው።

የጥምቀት በዓል በማይዳሰስ ቅርስነት ከተመዘገቡት ቅርሶች አንዱ መሆኑን በማስታወስም፤ ከዓመት እስከ ዓመት በርካታ ሕዝብ አደባባይ ወጥቶ ያከብረዋል ብለዋል።

የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑም ሆነ ያልሆኑ ዜጎች እሴታቸውን፣ ባህልና ትሩፋታቸውን ለማሳየት በዓሉን ይጠቀሙበታል ያሉት ቀሲስ ታጋይ፤ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች አልባሳት፣ ህብረ ዝማሬዎችና ባህላዊ ትውፊቶች የሚደምቁበት መሆኑን አንስተዋል።

ከተለያየ ዓለማት በዓላት በሚከበርበት በባህረ ጥምቀቱ ስፍራ በመታደም ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታቀርባቸውን ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓቶች እንደሚከታተሉም አመልክተዋል።

በዓሉ ትህትናና አብሮነት የሚገለጽበትና ታቦታቱ ወደባህረ ጥምቀቱ አውራ ጎዳናን አቋርጠው በሚሄዱበት ጊዜ ምዕመናኑ ታቦታቱን የሚያጅቡበት ነው ያሉት ቀሲስ ታጋይ፤ ከክርስትና እምነት ውጪ ያሉ ደግሞ ውሃ በማቀበል፣ ቦታ በመጥረግና አውደምህረትን በማጽዳት አብሮነትን የሚገልጹበት ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክሩበት በዓል ነው ብለዋል።

እንደ ቀሲስ ታጋይ ገለጻ፤ ጥምቀት በተለይ በክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሰረት ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ 30 ዓመት ሲሞላው በዕደ ዮሐንስ ወይንም መንገድ ጠራጊ ተብሎ በሚጠራው በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ የተጠመቀበት ዕለት የሚታሰብበት ነው።

የጥምቀት ከተራ ልክ እንደ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወርዶ እንደተጠመቀ ታቦታቱ በዋዜማው ከየመንበረ ክብራቸው ውሃ ወደተገደበበት ቦታ ወርደው በባህረ ጥምቀት እንደሚያድሩም አብራርተዋል።

የክርስቶስን መለኮታዊ ስልጣን እንደገለጸ ሁሉ ታቦታቱም ባርከው ሥርዓተ ቅዳሴ ተከናውኖ እና ሥርዓተ ጥምቀት ተፈጽሞ ወደ መንበረ ክብራቸው የሚመለሱበት የአደባባይ በዓል ሲሆን፤ በዚህ መልኩ ሃይማኖታዊ እሴቶቹ ሲከናወኑ ዜጎች ተሰባስበው በአንድነት የሚጓዙበትና ማህበራዊ መስተጋብራቸውን የሚያጠናክሩበት ዕድል ይፈጠራል ሲሉ አስረድተዋል።

ከምንም በላይ ኢትዮጵያዊያን ለሰላምና ለአብሮነት ዋጋ ሰጥተው ሊሰሩ እንደሚገባቸው ቀሲስ ታጋይ ገልጸው፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን ሲያከብር ሃይማኖታዊ ይዘቱንና መንፈሳዊነቱን በጠበቀ መልኩ ሊሆን እንደሚገባም አሳስበዋል።

# የሰው ልጅ እዳን የመሰረዝ ተምሳሌት

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ሐተታ**

"ጥምቀት" በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ ጥር 11 የሚከበር የኢየሱስ ክርስቶስን በዮርዳኖስ ወንዝ የመጠመቁን ምሳሌ የመፈጸም መንፈሳዊ በዓል ነው። በዚህ ቀን ዋዜማ ደግሞ የከተራ በዓል ይከበራል።

"ከተራ" ቃሉ ከተረ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን፣ መከተር፣ መከበብ፣ መገደብ የሚል ፍቺ አለው። ቃሉ ጥምቀት የሚካሄድበትን ውሃ መከበብን መገደብን፣ መከተርን ይገልጻል።

ከተራ የጥምቀት መዘጋጃ ነው። በከተራ ዕለት ታቦታት ከቤተ መቅደስ ወጥተው ውሃ ባለበት አካባቢ ያድራሉ። ሕዝቡም ከየአካባቢው እየተሰበሰበ ለመጠመቂያ በሚሆን ወንዝ ዳር ወይም በምንጭ አካባቢ ድንኳን ይተከላል፤ ዳስ ይጥላል። ወራጅ ውሃ ካለ እንዳይሄድ ይገደባል፤ ውሃውም ተባርኮ ለጥምቀት ይዘጋጃል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ በጣሊያንና አካባቢው ሀገረ ስብከት በቱርክ ኢስታንቡል ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን አገልጋይ፣ መምህር ዮሐንስ መንገሻ፣ "ጥምቀት" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወርዶ በዮሐንስ እጅ የፈጸመውን ጥምቀት መነሻ ያደረገ በዓል መሆኑን ያነሳሉ።

እርሳቸው እንዳሉት ጥምቀት ክርስቶስ የፈጸመው የጽድቅ ተግባር ነውና ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማርነውን ሥርዓት ለመፈጸም ክርስቶስ እንደተጠመቀ እኛም የምንጠመቅበት፣ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" የሚለውን መፅሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ለሚፈጸም የሚደረግ መንፈሳዊ ሥርዓት ነው።

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ፋንታ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ሩፋኤል ቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ቀሲስ ነቃ ጥበብ አዲሱ በበኩላቸው፣ በከተራ በዓል ታቦታት ከየቤተ መቅደሱና ከየአድባራቱ ወጥተው ወደተዘጋጀላቸው ስፍራ መሄዳቸው በብሉይ ኪዳን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ አውራጃ ወደ ዮርዳኖስ የመውረዱ ምሳሌ መሆኑን ጠቅሰው፣ "ጥምቀት" ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስ በአዳምና ሄዋን በኩል ለሰው ልጆች የሰጠውን የእዳ ፊርማ ለመደምሰስ ሲል በዮሐንስ እጅ የመጠመቁ ምሳሌ እንደሆነ ያብራራሉ።

ክርስቶስ ኢየሱስ ምሳሌ ያደረገው "ውሃ" ልብስን የሚያነጻ፣ እድፈትን የሚያፀዳ፤ ጥምን የሚያረካ ድሃ ሀብታም



ሳይል ሁሉም የሚያገኘው፣ ትልቅ ትንሽ የማይል ሁሉን ያማከለ ስለሆነ ውሃን መርጦ በማህፀነ ዮርዳኖስ ተጠምቋልና የክርስቶስ ቅርንጫፎቹ የሆንን ልጆቹ ይህንን እንፈጽማለን ብለዋል።

መምህር ዮሐንስ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ቤተክርስቲያን የሚከበሩ በዓላት መሠረታቸው ሰላም እንደሆነ ይናገራሉ።

መምህሩ እንዳሉት፣ የሰላም ሁሉ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የሰላም አምላክ ተብሎ ይጠራል፤ ሁሉም ቤተ ክርስቲያኗ የምታከብራቸው በዓላት ሰላምን ማዕከል ያደረጉ ናቸው። ልክ እንደ ሌሎቹ በዓላት ሁሉ የጥምቀት በዓልም የሰላም ማብሰሪያ ነው። ለዚህም ነው በዓሉን ለሚያከብሩ ሁሉ "እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ" የሚባለው።

በመጽሐፍ ቅዱስም "በጨለማ እና በሞት ጥላ ለሄደ ሕዝብ ሁሉ በክርስቶስ ጥምቀት ታላቅ ብርሃን የበራለት መሆኑ ተጽፏል። በመሆኑም፣ በጥምቀት የተጣላው ሊታረቅ፣ የተራራቀው ሊቀራረብ፣ የወደቀው ሊነሳ ይገባል። ይህም ትልቅ ማኅበራዊ ትርፍን ያስገኛል። እንደ ሀገርም ባህላችንን ለማየት ከሌላው ዓለም ለሚመጡ፣ እሴታችንን፣ ሃይማኖታዊ ባህላችንን የሚያሳይ፣ በቱሪዝም መስህብነቱም ለሀገር ኢኮኖሚው ፋይዳ ያለው ትልቅ በዓል ነው።

በዓላት ኢትዮጵያዊ እሴታቸውን ጠብቀው በራሳችን ወግና ሥርዓት ሲከበሩ ለሀገርም፣ ለቤተ ክርስቲያንም እንደ ሕዝብም ትልቅ ጥቅም አላቸው ያሉት መምህር ዮሐንስ፣ በዓሉን ስናከብር የተጣሉትን በማስታረቅ፣ የተረሱትን በማስታወስ እንጂ ነጭ ልብስ ለብሰን፣ ሲገኝ በልተን ጠጥተን እኛው ብቻ ደስተኞች ሆነን የምናሳልፈው ብቻ መሆን የለበትም ይላሉ።

ክርስቶስ አምላክ ሆኖ ሳለ ራሱን ዝቅ አድርጎ በባህረ ዮርዳኖስ መጠመቁ፤ ሁሉም ሰው ሊያገኘው ያለውም የሌለውም ደሃም ባለጠጋውም እኩል ሊያገኘው በሚችለው በውሃ መጠመቁ ትህትናን ሊያስተምረን ነው ያሉት መምህር ዮሐንስ፣ እንደ ሀገርም እንደ ቤተክርስቲያንም ክርስቶስ በሄደበት መንገድ ብንጓዝ የተሻለ ሕይወት ይሆንልናል ብለዋል።

የጥምቀት በዓል እርስ በእርስ የሚያጋምደን ነው ያሉት ደግሞ ቀሲስ ነቃጥበብ ናቸው። እርሳቸው እንዳሉት፣ በዓለ ጥምቀት በገጠርም በከተማም፤ በቆላም በደጋም ያለውን ሁሉንም ማኅበረሰብ የሚያሳትፍ በዓል ነው። አንዱ ከአንዱ የሚበልጥበት አንዱ ከአንዱ የሚያንስበት በዓል አይደለም። ሁሉም የየራሱን ባህላዊ ልብሱን ለብሶ ተከባብሮ፤ ተፋቅሮ፤ ተሳስቦ የሚያከብረው በዓል መሆኑ የተለያየ ቋንቋና ባህል ያለውን ሕዝብ ያስተሳስራል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያውያን በዓለም መድረክ ልዩ የሚደርገን የራሳችን የባህል መገለጫዎች አሉን፣ እነዚህን መገለጫዎቻችንን ይዘን በዓሉን በፍቅር ስናከብር ከመንፈሳዊ ትርፉ በተጨማሪ በዓሉ ለማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶቻችን መዳበር ለኢኮኖሚያችንም ጭምር ትልቅ ሚና ያለው ይሆናል።

በዓሉ ለቤተ ክህነትም ለመንግሥትም ትልቅ ዋጋ አለው ያሉት መምህሩ፤ በመላው ዓለም ለሚገኙ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ስጥምቀት ያልሆነ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በባህላቸው ደምቀው ሃይማኖታዊም ባህላዊም ሥነሥርዓቶችን የሚያከብሩበት መሆኑን ያስረዳሉ።

በጥምቀት በዓል አለባበሱ እንደየአካባቢው ይለያያል። የክትና የአዘቦት የአዘቦት አለባበስ አለ። ለበዓል የክት ይለበሳል። የቀደምት ኢትዮጵያዊያን ባህላዊ አልባሳት በአብዛኛው የሚዘጋጀው ከጥጥ ነው የሚሉት ዶክተር መስፍን፤ አዘገጃጀቱ ባህልንና እምነትን መሰረት ያደረገ ነው ይላሉ።

ቀሚስ፣ ኩታ፣ መቀነት፣ ጋቢ፣ ነጠላና ሌሎችም ከጥጥ የሚዘጋጁ ባሕላዊ አልባሳት የጥምቀት ዋነኛ ማጌጫ ናቸው። በበዓሉ ደምቀው የሚታዩ ልጃገረዶችም በርካታ ናቸው። በመሆኑም ባህሉንና ወጉን ጠብቆ ማቆየትና ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ተገቢ መሆኑን የመከሩት።

በአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከፍተኛ የቅርስ ጥናት ተመራማሪ የሆኑት መምህር መክብብ ገብረማርያም ደግሞ በበኩላቸው፤ ጥምቀት ሴቶች ጸጉራቸውን ሹሩባና ሌሎች ባህላዊ ቁንዳላዎችን ተቆንድለው ፣ እጅና እግሮቻቸውን በእንሶስላ አስጊጠው፤ አምባር፣ አልቦ፣ ድሪ፣ ጉትቻና በሌሎች ጌጣጌጦችን ተውበው የሚታዩበት የአደባባይ በዓል ነው ይላሉ።

ለጥምቀት በዓል ሕፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን እንደ ዕድሜ ክልላቸው "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" የሚለውን ስነቃል መሰረት በማድረግ ዘንጠው ይወጣሉ። ጥምቀት የሃይማኖት፣ የማንነት፣ የባህልና የውበት መገለጫ በመሆኑ አለባበሱም ልክ እንደዚያው እነደየአካባቢው ይለያያል ሲሉ ያስረዳሉ።

በጥምቀት በዓል የሃይማኖት አባቶች እንደቤተክርስቲያን ደንብ፣ ምዕመናኑ ደግሞ በባህላዊ አልባሳት ደምቀው መታየቱ በዓለም መድረክም ልዩ ያደርገናል የሚሉት መምህር መክብብ፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ነገስታት በዓመቱ ውስጥ የተሰሩትንና በቀጣይ የሚሰሩትን ሁነቶች በባህላዊ አልባሳት አጊጠው ለሕዝቡ በማስተዋወቅ ለልማት ስራዎች ተባባሪ እንዲሆኑ ይጠቀሙበት እንደነበር ታሪክ ምስክር መሆኑን ይናገራሉ።

የጥምቀት በዓል የሰዎች ውበት እንደጥቅምት አበባ የሚፈካበት፤ መጤ ባህሎች ለመከላከል፣ ባህላዊ ምግቦችን ለማዘጋጀት፣ ቀደምት የኪነጥበብ ውጤቶች ለማንጸባረቅ እና በኢትዮጵያ የሚሰሩ ባህላዊ አልባሳትን፣ ጌጣጌጦችንና ገበያ ለማሳደግ ምቹ አጋጣሚ መሆኑን ነው ያብራሩት።

በጥምቀት ወቅት በተለይ ከሚደምቁ ገበያዎች አንዱ የሽሮ ሜዳ የባህል አልባሳት ገበያ ነው። በገበያ ማዕከሉ ወይዛዝርትና ወጣት ሴቶች መተላለፊያ እስኪጠብ ድረስ ሞልተው ይገበያያሉ።

ለጥምቀት የተሰሩት አልባሳት አብዛኞቹ ቱባ ባህልን የጠበቁ የሀገር ቤት የጥበብ ስራዎች ናቸው። የራያ ቀሚስ ከመቀነት ጋር (ቦፌ)፣የጎንደር ጥበብ፣ የትግራይ ጥበብ (ጥልፍ)፣ የወሎ፣ የሸዋ፣የጉራጌና የበርካታ አካባቢዎችን ቱባ ባህል የያዙ አልባሳት ለገበያ ቀርበዋል። ከስምንት ሺ ብር እስከ ሁለት ሺህ ብር የሚጠራባቸው የሴቶች የባህል አልባሳት አሉ።

በገበያ ማዕከሉ ካገኘናቸው ሶስት ወጣቶች መካከል አንዷ ለመግዛት ያሰበችው አንድ የባህል ቀሚስ ነው። ቢሆንም ሁለቱንም ለመውሰድ ብታስብም ዋጋው እንደገመተችው አልሆነላትም፤ ብር አነሳት፤ ጓደኞቿ ‹‹ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት›› በማለት ከተሳሳቁ በኋላ ያላቸውን ብር አዋጥተው ያማራትን ቀሚስ ደስ ብሏት እንድትገዛ አድርገዋል።

በገበያ ማዕከሉ ውስጥ የባህል ልብስ ነጋዴ የሆኑት ወይዘሮ ሰናይት ፀጋዬ፤ ብዛት ያላቸው የባህል አልባሳት የሚሸጠው ለጥምቀት በዓል ነው ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

ደንበኞች ለጥምቀት በዓል የሚመርጡት አብዛኛው ጊዜ ቱባ ባህሉን የጠበቀ የጥበብ ሥራ እንደሆነም ያስረዳሉ፤ በብዛት ግን መራጮቹ ሴቶች ናቸው።

በዓላቶቻችን ለኢኮኖሚው የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ቀላል እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል የሚሉት ነጋዴዋ፤ ድንቅ ባህሎቻችንን በተለይ የበዓል ወቅት አለባበሶች ባህላዊና ትውፊታዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ የሚቆዩበትን መንገድ እያጠናከሩ መሄድ ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።



# ስምምነቱ የኢኮኖሚ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኢትዮጵያ ለሚገኙ የዓለም አቀፍ ተቋማትና የተለያዩ ሀገራት ወታደራዊ አታሼዎች ስለወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

በወቅቱ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን እንዳስረዱት፤ ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት እያደገ የመጣውን የሕዝብ ቁጥርና ኢኮኖሚ ምላሽ መስጠትን ዓላማ ያደረገ እንጂ ማንንም አካል ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ አይደለም።

ያለፈውን መኖር አንችልም ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ እያጋጠማት ያለው ወቅታዊ ችግሮች በመቋቋም ዘላቂ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት የምታደርገው ጥረት የፍላጎት ሳይሆን የህልውና ጉዳይ መሆኑን አጽንኦት የሰጡት አምባሳደር ሬድዋን፤ ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር የፈጸመችው ስምምነት ዓለም አቀፍ መርህ የሆነውን ራስን በራስ የማስተዳደርና የግዛት አንድነትን ባከበረ መልኩ የተከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መሆኑንና አሁን ላይ 120 ሚሊዮን ገደማ መድረሱን አመላክተው፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥም 150 ሚሊዮን እንደሚገባና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚም እያደገ በመሆኑ የባህር በር ጉዳዩ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ መሆኑን አምባሳደር ሬድዋን አንስተዋል።

አምባሳደር ሬድዋን እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዓመታት ያለ ባህር በር በመቆየቷ በጂቡቲ ወደብ በኩል የገቢ ወጪ ንግዷን እያከናወነች ቆይታለች።

አሁን ካለው ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ተጨማሪ የወደብ አማራጮችን መፈለግ ግድ ስለሚል ስምምነቱ ተፈጽሟል ብለዋል።

በተጨማሪም በቀይ ባህር አካባቢ የየመን ሁቲዎች ጥቃትን በተመለከተ ሰሞኑን እየተፈጠረ ካለው ችግር ጋር ተያይዞ በጂቡቲ ወደብ አካባቢ የተባባሰ ጥቃት ከተፈጸመ ኢትዮጵያ ሌላ የወደብ አማራጭ ስለሌላትና ተጨማሪ የባህር በር አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱንም አመላክተዋል።

በዚህም በኢትዮጵያና በሶማሊላንድ መካከል የተደረገው ስምምነት ተጨማሪ የወደብ አማራጮችን ለማግኘት የተደረገ እንጂ የማንንም ጥቅም ለመንካት እንዳልሆነ አስታውሰዋል።

ስምምነቱ በቀጠናው የሚገኙ ሀገራት በጋራ እንዲሰሩና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲያድግ የሚረዳ በመሆኑ ከተቃውሞ ይልቅ ድጋፍ ሊሰጠው በተገባ ነበር ሲሉ አስረድተዋል።

የተደረሰውን ስምምነት ተከትሎ ከዓውድ ውጪ የሆኑ የተሳሳቱ መረጃዎች እየተሰራጩ መሆናቸውን የገለጹት አምባሳደሩ፤ የባህር በር ጉዳይ ለኢትዮጵያ የፍላጎት ሳይሆን የህልውና ጉዳይ መሆኑን ሊታወቅ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሰላምና ፀጥታ የሕይወት መስዋዕትነት እየከፈለች መሆኗን ጠቅሰው፤ ከሶማሊያም ሆነ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ትብብር እንደምታደርግ አረጋግጠዋል።

በማብራሪያው የመከላከያ የውጭ ግንኙነትና ወታደራዊ ትብብር ዋና ዳይሬክተር ሜጀር ጀነራል ተሾመ ገመቹ እና በኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል አምባሳደር ፍሰሃ ሻውል ተገኝተዋል።



# ኢትዮጵያ ስጀመረችው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ያሉት ከንቲባዋ፤ በለውጥ ሂደቱ ውስጥ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሀገራዊ ጥሪን በማክበር የራሳቸውን አሻራ እያኖሩ እንደሆነና ወደ ፊት "በወቅቱ እኔም ነበርኩበት፣ ሀገሬን በትልቅ ደረጃ አስተዋውቄያለሁ" ብለው የሚናገሩትን ታሪክ እንደሚጽፉ ተናግረዋል፡፡

ቆይታችሁ በሀገራችሁና በሕዝቡ አኗኗር እንድትኮሩ ያደርጋችኋል በማለት፤ "ኢትዮጵያን ከእናንተ በላይ ሊያስተዋውቅ የሚችል የለም" ብለዋል፡፡

በቆይታቸው በተለይም ነገ የሚከበረውን የጥምቀት በዓል ጨምሮ በርካታ ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ ሁነቶችን በማየት ብዙ ቁምነገር እንደሚያተርፉ ገልጸው፤ ወደመጡበት ሀገር ሲመለሱ ኢትዮጵያን የበለጠ እንዲያስተዋውቁም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በበኩላቸው፤ ጥሪው በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን የእረፍት ጊዜያቸውን ተጠቅመው የትውልድ ሀገራቸውን ባህሎችና ትውፊቶች እንዲገነዘቡ እንዲሁም ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ትስስር እንዲፈጥሩ በሚያስችሏቸው ሁነቶች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ወደ መኖሪያ ሀገራቸው ሲመለሱ ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቁ አምባሳደሮች እንዲሆኑ ለማስቻል እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሚና የማይተካ እንደሆነ ገልጸው፣ ጥሪውን አክብረው የመጡ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን በሚገባ አውቀው ለሌሎች የማሳወቅ እድል እንዳላቸው አስታውቀዋል።

መንግሥት በሰፊው እያከናወነ ላለው የሰላምና የዲፕሎማሲ ሥራ የጎላ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱም ሚኒስትሯ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

Zemen Express Delivery
on time every time



ዘመን ባስ ኢትዮጵያ ትራንስፖርት አገልግሎት
Zemen Bus Ethiopia Transport Service

ለክቡራን ደንበኞቻችን እና ለመላው ኢትዮጵያዊያን
እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ እያልን በማንኛውም ጊዜ ወደ
ሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል ጉዞ ለማድረግ ሲያስቡ ምርጫዎ ዘመን ባስ ይሁን

በአጭር ቁጥር 6162 ነፃ ጥሪ በመጠቀም
ባሉበት ሆነው ትኬትዎን በባንክ ይቁረጡ

Zemen Ethiopia
ዘመን ባስ - ኢትዮጵያ
Zemen Bus - Ethiopia

በተጨማሪም ድርጅታችን የጥቅል
መልዕክቶችን ወደ ሁሉም የሐገራችን
የክልል ከተሞች በጥራት እና በቅልጥፍና
ማድረስ መጀመሩን በደስታ እንገልጻለን፡፡

መረጃ ለማግኘት
በአጭር ስልክ ቁጥር 6162
አሁኑኑ ይደውሉ

በዘመን ይላኩ በዘመን ይቀበሉ!!

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጥምቀትን በበዓሉ እሴቶች!

መንፈሳዊ በዓላት ዘመናት ተሻግረው ዛሬ ላይ እሴቶቻቸውን ጠብቀው መገኘት የቻሉት የሃይማኖቱ ተቋማት እና በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች ተገቢውን ጥበቃ እና እንክብካቤ ስላደረጉላቸው እንደሆነ ይታመናል። የወደፊት ቀጣይ ዕጣ ፈንታቸውም በዚሁ እውነታ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑም መገመት የሚከብድ አይደለም።

በተለይም እንደኛ ያሉ የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ምስረታ ታሪክ ያላቸው ሀገራት በአንድም ይሁን በሌላ ለማንነታቸው ግንባታ አቅም የሆኑ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶቻቸውን የሚያከብሩባቸው በዓላት ባለቤት መሆናቸው የማይቀር ነው።

እነዚህን በዓላት ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ እሴቶቻቸውን ጠብቆ ለመጪዎቹ ትውልዶች ማስተላለፍ እና እንደ ሀገር ከፍ ያለ ኃላፊነት የሚጠይቅ ፣ የሁሉንም ዜጋ ንቁ ተሳትፎ የሚፈልግም ነው። እውነታው በዚህ ዘመን ካለው የእሴቶች መፋለስ ስጋት አንጻርም ማንነትን የመጠበቅ ያህል የሚታሰብ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ እነዚህ ዘመን ተሻጋሪ በዓላት የአንድ ማኅበረሰብ የማንነት አሻራ ከመሆን በላይ የሰው ልጆች የጋራ እሴት መገለጫ ናቸው በሚል እውቅና እና ጥበቃ እንዲደረግላቸው እያደረገ ነው። በዚህም ረጅም መንገድ እየተሄደ ነው።

በዚህ ሂደት ሀገራችን እስካሁን 16 /የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ/ ቅርሶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስመዝገብ ችላለች። ከነዚህም በየዓመቱ በመላ ሀገሪቱ በኦርቶዶክስና ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ተከታዮች ዘንድ በድምቀት በአደባባይ የሚከበረው የጥምቀት በዓል አንዱ ነው ።

በዓሉ ከሁሉም በላይ የሰላም በዓል መሆኑ ፤ ከዚህም ጋር አብረው የሚነሱት የበዓሉ ዋነኛ እሴቶች ከሆኑት ትህትና ፣አብሮነት ፤ወንድማማችነት እና ኅብረ ብራዊነት ላገኛው አለም አቀፋዊ እውቅና ዋነኞቹ መሰረት ናቸው።እውቅናውን አስቀጥሎ ለመሄድም ወሳኝ ናቸው።

እነዚህ እሴቶች ከዚህም ባለፈ በማኅበረሰባችን የማንነት ግንባታ ውስጥ የጎላ ስፍራ ያላቸው ናቸው። አሁን በብዙ እየተሸረሸረ ያለው ማኅበራዊ ማንነታችንም የነዚህ እሴቶች ህያው አሻራ መገለጫ አድርገው የሚወስዱ ብዙ ናቸው። አሁን ላለንበት ችግር የተዳረግነውም ለነዚህ እሴቶች በቂ ጥበቃ ባለማድረጋችን ነው።

እነዚህ እሴቶች እንደ ሀገር ለመጣንባቸው ረጅም ዘመናት ያበረከቱ አስተዋጽኦ ከፍያለ እንደሆነም፤ ዛሬም ላይ እንደሀገር እያጋጠሙን ያሉ ፈተናዎችን በጽናት ለመሻገር ለምናደርገው ጥረት ትልቅ አቅም በመሆን የጥንካሬያችን ምንጭ እንደሆኑም ይታመናል።

አሁን ያለው ትውልድ እንደ ሀገር እያጋጠመው ካለው የልዩነት ትርክትና ትርክቱ እያስከፈለን ካለው ያልተገባ ዋጋ አንጻር እነዚህን እሴቶች የመጠበቅ ኃላፊነቱ ከፍ ያለ ነው ።እያንዳንዱ የእለት የህይወት መስተጋብሩ ውስጥ ስፍራና ጊዜ ሰጥቶ ሊተገብረው የሚገባ ነው።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ በዓሉ የሰላም በዓል ከመሆኑ አኳያ፤ ለራሱ የውስጥ ሰላም ሆነ አጠቃላይ ለሆነው ለማኅበረሰቡ ሰላም ተገቢውን ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ለሰላም ዘበ መቆም፤ ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅበታል።

የበዓሉን መንፈሳዊ ይዘት በአግባቡ ተረድቶ ፤መረዳቱን አሁን ካለው ተጨባጭ ሀገራዊ እውነታ ጋር በማስታረቅ፤ ራስን የችግር ሳይሆን የመፍትሄ አካል ማድረግ ወደሚያስችል፤ የመንፈሳዊ ማንነት ልዕልና ሊያመራ/ሊጓዝ ይገባል።

ትውልዱ መንፈሳዊ በዓላት በአደባባይ ከመከበራቸው አንጻር የሚፈጥረው ድምቀት፤ በዓላቱ በዋናነት የያዟቸውን መንፈሳዊ እሴቶች እንዳይጋርዷቸው መጠንቀቅ ፤ ከሚፈጥሩት የአደባባይ ድምቀት በላይ ሊፈጥሩት ለሚገባው መንፈሳዊ መነቃቃት ትኩረት መስጠትም ይገባል።

ይህንን ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው መንፈሳዊ በዓላት ትርጉም ሊኖራቸውና ድምቀታቸውም የእውነት ሊሆን የሚችለው፤ ለዚህ ደግሞ የመንፈሳዊ በዓሉ ባለቤት ምእመናን በሁለንተናዊ መልኩ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።ጥምቀትም ጥምቀት የሚሆነው በዚህ መልኩ ብቻ ተዘጋጅተን ስናከብረው ነው!።


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጥምቀትን በዓል ከማክበር ጎን ለጎን ለሰላም ዘብ እንቁም

**ትንሳኤ አበራ**

የጥምቀት በዓል በወርኃ ጥር በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በልዩ ልዩ ይከበራል፡፡ በዓሉ የሚከበርበት ዋና ዓላማም ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በሰው እጅ የተጠመቀበትና ለሰው ልጆች ሁሉ ትህትና እና ፍቅርን ያስተማረበትን ቀን ለማሰብ ነው፡፡ በዓሉን መላ የእምነቱ ተከታዮች በየአብያተ ክርስቲያናት በሚካሄድ በተለያዩ ሥነሥርዓቶች በድምቀት ያከብሩታል፡፡

በዓሉ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ዘንድ በአደባባይ በድምቀት ይከበራል፡፡ በየዓመቱ ጥር 11 የሚከበረው ይህ በዓል በዋዜማው የከተራ በዓልን በማክበር ይጀምራል፡፡ በከተራ ዕለት ታቦታት ከየአድባራቱ ወጥተው በቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች እና በምእመኑ በደማቅ ሥነሥርዓት ታጅበው በውሃ አካላት ዳርቻ በሚዘጋጁላቸው ቦታዎች ያመራሉ፤ በዚያው ያድራሉ፡፡ ታቦታቱ በሚገኙበት የወንዝ ዳርቻዎች የተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓቶች ይከወናል፡፡

በማግስቱ ጠዋት የጥምቀት በዓል ሥነሥርዓት ይከበራል፡፡ የእምነቱ ተከታዮች ከጥምቀት ሥነሥርዓቱ በተጨማሪ በልዩ ልዩ ባህላዊ ቀኑን ሲያደምቁት ውለው ታቦታቱ ወደየመጡበት ደብር ይመለሳሉ፡፡

ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓት ሲከበር የኖረው ይህ በዓል፤ ከሃይማኖታዊው ሥርዓቱ ባሻገር ምእመኑ ማህበራዊ እሴቶቹና መስተጋብሩ የሚያጠናክርበት ነው፡፡ ይህም የጥምቀት በዓል በሁሉም ማህበረሰብ ተጠባቂና ተናፋቂ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ጥምቀት ከሌሎች የአደባባይ በዓላት የተለየ ድባብ ያለው ሲሆን፣ ለእዚህም ልዩ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ ከአለባበስ ጀምሮ እስከ ውበት አጠባበቅ ድረስ ሁሉም ሰው በሚባል ደረጃ ድምቅ ፍክት ብሎ የሚታይበት ነው፡፡ ይህም ‹‹ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ›› የሚለውን የአበው አባባል እውነትነት ፍንትው አድርጎ ያመለክታል፡፡

ከከተራ ዕለት ጀምሮ በዓሉን ለማክበር አምረው እና ተውበው ከየቤቱ የሚወጡ እናቶች ፣አባቶች፣ወጣቶች እና የበዓሉ ውበትና ድምቀት ይሆናሉ፡፡

ለጥምቀት የክት ልብስ ይለበሳል፤ አዳዲስ ልቦሶች ይገዛሉ፤ ይህን ማድረግ ያልቻለም ያለውን አጥቦና ተኩሶ ይለብሳል፡፡ የዘመኑ ወጣቶች ደግሞ አለባበሱን ከቀደመውም በላይ እያደረጉት መጥተዋል። ጓደኞሞች፣ እህትማማቾች ወንድማማቾች ወዘተ አንድ አይነት የባህል ልብስ በመልበስ ወደ አደባባይ ይወጣሉ፡፡

ጥምቀት ሲነሳ መቼም የማይዘነጋው ጎበዛዝቱ ለቆነጃጅቶቹ የሚወረውሩት ሎሚ ነው፡፡ የሎሚ ውርወራ ደግሞ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባሕላዊ የመተጫጨት ዘዴ ተደርጎ ይወሰዳል። በተለይ በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍሎች በወጣቶች ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ ወጣቶች የሚተያዩበትና የሚተጫጩበት በመሆኑ አንድ ጎረምሳ ለወደፊት የትዳር አጋር እንድትሆን ለፈለጋት ኮረዳ ሎሚ በመወርወር የእርሱ እንድትሆን የሚጠይቅበትም ነው፡፡ በበዓሉ ላይ ተያይተው ተጫጭተው ለትዳር የበቁ ብዙዎቹ ምስክሮችም አሉ፡፡

በዓሉ ለወጣቱ ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች በርካታ ትዝታዎችን ጥሎ የሚያልፍ ነው፡፡ ከልጅ እስከ አዋቂ በልዩ ሁኔታ የሚታደሙበት በዓል እንደመሆኑ በዓመቱ ‹አምና ይሄኔ› እየተባለ በትዝታ ጭምር እስከ መታወስም ይደርሳል፡፡ በተለይ በመዲናችን በአዲስ አበባ በጃንሜዳ የሚከበረው የጥምቀት በዓል ልዩ ትዝታን የሚያጭር እንደሆነ ብዙዎች ይመሰክራሉ። በጃንሜዳ ከሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ባሻገር የሀርሞኒካ ጨዋታ፣ የተለያዩ ባሕላዊ ጭፈራዎች እና መሰል ሁነቶች ይከወናሉ፡፡

አሁን አሁን የጥምቀት በዓል ቀደም ባሉት ጊዜያት ይከበር ከነበረው የአከባበር “ስታይል” ለየት ባለሁኔታ እየተከበረ ይገኛል፡፡ ሀገሪቱ ያላት ቱባ ባሕል የሚታይበትም ጭምር እየሆነ ነው፡፡ የበዓሉ ታዳሚዎች በተለያዩ የባሕላዊ አልባሳት ደምቀው በጓደኛነት፣ በቡድን፣ በቤተሰባዊነት፣ በማህበር፣ በአንድነት አንድ አይነት ልብስ በመልበስ ለየት ብለው የሚታዩበት ፤ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የሚሳተፉበት ህብረ ብሔራዊ አንድነት የሚገለጹበት ነው፡፡

የጥቀምት በዓል ፊቱንም ቱሪስቶችን በመሳብም በእጅጉ ይታወቃል፡፡ እንደ ጎንደር ባሉ ቦታዎች በዓሉ በልዩ ሁኔታ በሚከበርባቸው አካባቢዎች በርካታ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ወደ አካባቢዎቹ ይተማሉ፡፡

የጥምቀት በዓል የዓለማችን የማይዳሰስ ቅርስ (Intangible world heritage) ሆኖ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) ታኅሣሥ 1 ቀን 2012 ዓ.ም መመዝገቡ ይታወሳል፡፡ ይህን ተከትሎም የቱሪስቶችን ቀልብ በእጅጉ በመሳብ የሚታወቀው ይህ የጥምቀት በዓል የቱሪስት መስህብነቱ እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህ በዓል የኛ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ዓለም አቀፍዊ እንደመሆኑ በበዓሉ ለመታደም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት በርካታ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን እየገቡ ይገኛሉ፡፡

የዘንድሮ የጥምቀት በዓል በውጭ ሀገራት የሚኖሩት የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያ የሚገኙበት እንደመሆኑ ለየት ባለ መልኩ እንደሚከበር ይጠበቃል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጥሪ የተደረገላቸው እነዚህ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን አባላት በዓሉን ለማክበር ወደ ሀገራቸው መግባት ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ይህም በበዓሉ የሚገኙ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እንዲጨምር እንደሚያደርግ ይጠበቃል፡፡

በበዓሉ ላይ ለመታደም ሀገር አቋርጠው የመጡ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች በዓሉን በሰላም አክብረው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ለማድረግ መላ ኢትዮጵያውያን ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

ለእዚህም ከጥንት ጀምሮ የምንታወቅበት ኢትዮጵያዊ የእንግዳ ተቀባይነትና መስተንግዶ ባሕላችን በዚህ ጊዜም ጎልቶ መታየት አለበት። እንግዶቻችንን በሰላም ተቀበልን በማስተናገድ በበዓሉ የማይረሳ ትዝታን ይዘው እንዲመለሱ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ባለፉት ዓመታት በስፋት እንደተስተዋለው ለጥምቀት በዓል በድምቀት መከበር አስተዋጽኦ እያደረጉ ካሉት አካላት መካከል ትልቁን ሚና እየተጫወተ ያለው ወጣቱ ነው፡፡ ወጣቱ ከበዓሉ አስቀድሞ የታቦታቱን የማደሪያ ቦታ፣ ታቦታቱ የሚጓዙባቸውን መንገዶች ከማጽዳት አንስቶ፣ ስጋጃ በማንጠፍ፣ ቄጤማ በመጎዝጎዝ እና የበዓሉን ታዳሚዎች በሥርዓት በማስተናገድ ፤ ከጸጥታ አካላት ጋር በመተባበር በዓሉ በሰላም እንዲከበር እያደረገ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህን ሚናውን ዘንድሮም አጠናክሮ ማስቀጠል ይኖርበታል፡፡

ወጣቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ ያሳየውን ትህትና እና ፍቅርን በማሰብ ኢትዮጵያዊ እሴቶችን በመላበስ ሰላም ከማስፈን አንጻር ብዙ ሥራዎች መስራት ይጠበቅበታል፡፡

እንደዚህ አይነት የአደባባይ በዓላት በሰላም ተከብረው እስኪጠናቀቁ ድረስ የሁሉንም ሰው ርብርብ ይጠይቃሉ፡፡ የዚህ በዓል በሰላም መከበር የማይጥማቸው እኩይ አላማ ያላቸው አካላት ደግሞ በተገኘው አጋጣሚ ተጠቅመው ፖለቲካዊ አጀንዳቸውን ለማራመድ ሊፈልጉ ይችላሉ። ስለሆነም የበዓሉ ታዳሚዎች በዓሉን በድምቀት ለማክበር ከሚያከናውኑት ተግባር በተጨማሪ በዓሉ በሰላም እንዲከበር ርብርብ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። መልካም በዓል!!

# መንፈሳዊ በዓላት መንፈሳዊነታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ ?

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

መንፈሳዊነትና የፖለቲካ እሳቤ ትንታኔዎች የሁለት ዓለም ከርሰ ምድሮች ናቸው፡፡ በእንዴትም ያለ የላቀና የዘመነ ሀሳብ ቢዳሰሱ አንዱ በአንዱ ውስጥ ህልውና የለውም፡፡ የጨለማና የብርሀን ያክል ልዩነት ግዝፈት ያላቸው ወዲያና ወዲህ ርዕዮተ አለሞች ናቸው፡፡

መንፈሳዊነት የመጀመሪያ ተልዕኮው ፈጣሪን ማክበር ነው፡፡ የፖለቲካ አስተሳሰብ ከዓለማዊ መሻት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ በእኚህ ሁለት የተራራቁ እሳቤዎች ውስጥ አንዱን በአንዱ ውስጥ አኑሮ አጀንዳ መፍጠር ለሰማዩም ለምድሩም የማይበጅ እኩይነትን መፍጠር ነው፡፡ በሕገ ዶግማና ቀኖና በሚተዳደር ሀይማኖት እና በተጻፈ ሕገመንግስት ስር በቆመ ፖለቲካ መሀል የሰላምና የኢትዮጵያዊነት ቁርኝት ካልሆነ ሌላ ነውጥ ፈጣሪ አስተሳሰቦች የማይስተናገዱባቸው ናቸው፡፡

በአጭር ቃል መንፈሳዊ በአል ማለት መንፈሳዊ ዓላማ ያነገቡ ሰውን ከፈጣሪና ፈጣሪን ከሰው ጋር የሚያገናኙ የጸሎት፣ የአምልኮ እንዲሁም የምስጋና እና የምጽዋት በዐላት ናቸው፡፡ ከዚህ አግንነን ካየነው ደግሞ ስለሀገርና ስለሕዝብ የሚጸለይባቸውና የሚጾምባቸው ምህላም የሚያዝባቸው ሁሉን አቃፊዎች ናቸው፡፡

እኚህ በአላት በእንዴትም ያለ መልኩ የአንድ ወገንና የአንድ ቡድንን ዓላማ ደግፈው ሌላውን ሊኮንኑ ዶግማና ቀኖና አይፈቅድላቸውም፡፡ ወይም ደግሞ ጊዜና አጋጣሚን እየጠበቁ የአንድን የሆነ አካል ዓላማ አያራግቡም፡፡ ይህ በፍጹም የሚጠበቅ አይደለም፡፡

የፊታችን ዓርብና ቅዳሜ የሚከበረው የጥምቀት በዐል ሰላም ሰባኪ ከሆኑ የሕዝብ በአላት መካከል አንዱ ነው፡፡ ላለፉት በርካታ ዓመታት ሀገርና ትውልድን በስነምግባርና በመቻቻል እሴት ሲቀርጽና ሲያስውብ የኖረ የአደባባይ በዐል ነው፡፡ ኢትዮጵያውያንን በአንድ ተሰባስበው ከመንፈሳዊነት ባለፈ ፍቅርና አንድነትን የሚያወራረሱበትም ነው፡፡

ሀይማኖታዊ በዐላት ትውልዱ በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ ባሕልና ወጉን፣ አንድነትና ወንድማማችነቱን አስጠብቆ እንዲሄድ የጎላ ሚና ተጫውተዋል፡፡ መንፈሳዊ በረከታቸው እንዳለ ሆኖ ሀገራዊ የአብሮነት ውርርስና ቅብብሎሻቸውም እኩል ሊወሳ የሚችል በጎ ገጽታቸው ነው፡፡ የሀገርን ገጽታ ከመገንባትና ለውጪው ማሕበረሰብ ኢትዮጵያን ከማስተዋወቅ አኳያ ይሄ ነው የማይባል ሚና አላቸው፡፡ ይሄ ሀገራዊ ፋይዳቸው ታይቶም ነው በዩኒስኮ ላይ በቅርስነት የተመዘገቡት፡፡

የዓለም አቀፉ የባሕልና የቅርስ ተቋም አንድን መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ በአል በዓለም አቀፍ ቅርስነት ሲመዘግብ የራሱን ሕግና መርህ ተከትሎ ነው፡፡ ከመርሆቹ አንዱ ሰላም ፈጣሪነት ነው፡፡ ጥምቀትም ሆነ ሌሎች ኢትዮጵያዊ በአላት በዩኒስኮ በቅርስነት ሲመዘገቡ ስለሀገርና ሕዝብ ያላቸው ሰላማና በጎ አሻራ ታይቶና ተጠንቶ ነው፡፡ የጥምቀት በዐል ለሀገርና ለሕዝብ በተለይ በሰላም ዙሪያ ያለው አንድምታ ደማቅ መሆኑ ታምኖ በቅርስነት ሰፍሯል፡፡

ጥምቀት የሰላም ምልክት..የኢትዮጵያዊነት ቀለም ነው፡፡ ትውልዱን በጨዋነት ያራመደ፣ ምዕመናኑን በእምነትና በእውነት ያቆመ፣ ሀገርን በበረከትና በጸጋ ያሻገረ በዐል ነው፡፡ አሁን ላይ ላሉብን ሀገራዊ ውጥንቅጦች ሰላም ከመስበክና እርቅና ተግባቦትን ከመመስከር አኳያ የበአሉ ሚና የማይናቅ ነው፡፡

ጥምቀት የእግዚአብሄር ክብር የሚገለጥበት፣ በታቦተ ሕጉ ፊት አማኙ ስለተደረገለትና ስለሚደረግለት እልል የሚልበት፣ ከተከተረ እና በቡራኬ ከበቃ ጸበል ሕይወቱን የሚያለመልምበት ነው፡፡ እኚህ ሁሉ ሂደቶች የበዐሉን ዓላማና ይዘት የሚገልጹ ለሀገርና ሕዝብ ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያዊነት አማኝነት እንደሆነ በፈጣሪና በኢትዮጵያውያን መሀል ያለውን የመተማመን ትስስር አጉልቶ የሚያሳይ በዐል ነው፡፡,ይሄ የሰላም ምልክት የሆነ በዐል በምንም አይነት መልኩ ተፈጥሮአዊም ሆነ ሀይማኖታዊ መልኩን ስቶ ለማይሆን እኩይ ዓላማ መጠቀሚያነት ሊውል አይገባም፡፡

> **እርቅና ይቅርታን ከትዕግስትና ከስክነት ጋር እናውራበት፡፡ ውይይትና ምክክርን ከወንድማማችነት ጋር እናጽናበት፡፡ ይሄ ሲሆን ነው በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ግዳይ ጥለን በፈጣሪና በፍጡራን መሀል ባለማዕረግ የምንሆነው**

አንዳንዶች እንዲህ ያለውን ሀይማኖታዊና ኢትዮጵያዊ ቀለም ያለው በዐል ለእኩይ ዓላማ ማስፈጻሚያነት ሊጠቀሙት ሲዳዳቸው ይስተዋላል። መንፈሳዊም ይሁን ዓለማዊ በዐላት ሀገርና ሕዝብን በተመለከተ ሚናቸው አንድ ነው፤ ፍቅርን መስበክ፣ አብሮነትን ማጽናት ነው፡፡

ትውልዱ ከለመደው መንፈሳዊነት እንዳይወጣ ማጽናት እንጂ ዘርና ብሔር ተኮር በሆነ የእኩያን ፍላጎትና ዓላማ ፈሩን እንዲስት ማድረግ አይገባም፡፡ ለዘመናት በዐላት ሲመጡ ጾምና ጸሎትን የመሳሰሉ የለመድናቸው የአምልኮ ስርዐቶች አሉ፡፡ ትውልዱ ሰውና ኢትዮጵያዊ የሆነው በዚህ ስርዐት ተገርቶ ነው፡፡

ኢትዮጵያዊነት የአማኝ ሀገር የተባለው በዚህ እውነት በኩል ነው፡፡ በዐላት አላማቸውን ሲስቱ አንድ ወገንን ብቻ አይደለም የሚጎዱት እንዳለ ትውልዱን ነው የሚጎዱት፡፡ የትውልድ ጉዳት ደግሞ የሀገርና የመጪው ጊዜ ጉዳት ነው፡፡ በሕገ እግዚአብሄር ተገርቶ በጨዋነት ያደገ ትውልድ የሚያውቀውና ያደገበት በዐለ አምልኮ ለእኩይ ዓላማ ሲውል ሲያይ ውደ ስህተት ነው የሚገባው፡፡

ሀይማኖታዊ በዐላት አንድና አንድ ዓላማቸው እግዚአብሄርን መስበክ ነው፡፡ እግዚአብሄር ደግሞ በፍቅርና በእርስ በርስ መዋደድ ውስጥ የሚሰብክ ነው። በስርዐት የተገነባው የትውልዱ ቤት እንዳይፈርስ፣ በእምነትና በእውነት የጸናው የኢትዮጵያዊነት ስማችን እንዳይጎሽ ፈር ከሳተ እኩይ ዓላማ መቆም አለብን፡፡

እንደ ጥምቀት ያሉ በሰላም ሚዛን ስለሰላም ባዋጡት አስተዋጽኦ እውቅና የተቸራቸው በዐላት ከዚህ ተልኳቸው እንዳይጎሉ ዓለም አቀፉ የቅርስ ጥበቃ ያሳስባል፡፡ አንድ ጊዜ ተመዝግበው የሚያበቁ አይደሉም፡፡ በየዓመቱ ሲከበሩ ዓላማና እያደረጉ ያሉት አስተዋጽኦም ይገመገማል፡፡ እንደዛ ካልሆነ የቅርስነት እውቅናቸው ሊሰረዝ ሁሉ ይችላል፡፡

የሰላም ዋጋ በተመን የሚሰላ አይደለም። አሁን ያለችው ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላይ ሰላም ያስፈልጋታል፡፡ ሰላም ብቻ አይደለም ሰላምን አጽንቶ የሚያቆይ ማህበራዊ ስርዐት ግድ ይላታል። ከስርዐቶቻችን መካከል ደግሞ ጥምቀትና መሰል የአደባባይ በዓላት ሰፊውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ በጥምቀት የሚመጣው የአማኝ ቁጥር እጅግ የበዛ ነው፡፡ በዛ ቀንና በዛ አማኝ መሀል የምትነገር የፍቅር ቃልም ሆነች የጥላቻ ንግግር ብዙዎች ዘንድ የመድረስ እድሉ ሰፊ ነው፡፡

ጥምቀትን ፍቅርን እንስበክበት፡፡ አንድነትና አብሮነትን እንናገርበት፡፡ እርቅና ይቅርታን ከትዕግስትና ከስክነት ጋር እናውራበት፡፡ ውይይትና ምክክርን ከወንድማማችነት ጋር እናጽናበት፡፡ ይሄ ሲሆን ነው በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ግዳይ ጥለን በፈጣሪና በፍጡራን መሀል ባለማዕረግ የምንሆነው፡፡ በጾምና ጸሎት በምስጋናም በፈጣሪ ፊት መቆማችን ትርጉም የሚያገኘው እንዲህ ባለው በጎ ስራ ስንበረታ ነው፡፡

የጥምቀት በዐል ከሰላም እና አንድነትን ከመስበክ አኳያ የላቀ መድረክ እንደሆነ መናገር ይቻላል፡፡ በታቦቱ ፊት ለአምልኮ ስንቆም፣ በባሕሩ ዳር ጸበል ሲነካን ዓመት ዓመት አድርሰን ብለን ስንመራረቅ ደስታ የዋጀው ውስጣችን የሚሰርግ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አለ፡፡

እዚህ ጋ ማስታወስ የምፈልገው አንድ ጉዳይ ቢኖር ታቦቱም ሆነ ጸበሉ ከስጋችን አልፎ ነፍሳችን ላይ የሚያርፈው ልባችን ውስጥ ባስቀመጥነው እምነትና እውነት በኩል ነው፡፡ ካለፍቅር፣ ካለይቅርታ፣ ካለወንድማማችነት በፈጣሪ ፊት የምናገኘው ሞገስ የለም፡፡ ዓመት ዓመት አድርሰን ብሎ መጸለይ እጅግ መልካም ነገር ነው፡፡

ግን ዓመት ዓመት ለመድረስ ኢትዮጵያ ደህና መሆን አለባት፡፡ የሀገርና የወገን ሰላም መጠበቅ አለበት። ፍቅርን ሰብከን፣ አንድነትን አጽንተን የበኩላችንን ስናዋጣ ነው የምንደርሰው፡፡ ደግሞም ዓመት ዓመት የምንደርሰው በአፋችን ፍሬ በኩል ነው፡፡ ስለሰላም የምናወራ ከሆነ የአፋችን ፍሬ ወደነገ እንድንሸጋገር መንገድ ይሰጠናል። የምንራገምና ስለጥላቻ የምናወራ ከሆነ የአፋችን እኩይ ቃል የነገ መንገዳችንን ይዘጋብናል፡፡

ይሄን አስመልክቶ ታላቁ መጽሀፍ ቅዱስ በምሳሌ መልዕክቱ ላይ ‹ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ውስጥ ናቸው› ይለናል፡፡ በዛም በምሳሌ መልዕክት ላይ ‹ሰው ከአፉ ቃል በጎውን ይበላል› የሚል ጥቅስ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ስለሀገራችን የምናስበው፣ የምንናገረው ነው ነገ ላይ ዓመት ዓመት የሚያደርሰን፡፡

በአሁኑ የጥምቀት በዐል ላይ ጥልና ክርክርን፣ ጥላቻና መለያየትን የሚሸሩ ስብከቶች፣ መልዕክቶች ናቸው ከጦርነት ታድገው ለነገ ብርሀን የሚያጩን፡፡ ዓመት ዓመት አድርሰን ብለን ስንጸልይ በአፋችን ምን እየተናገርን፣ በስብከቶቻችን፣ በመልዕክቶቻችን ምን እያስተላለፍን እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል፡፡

መንፈሳዊ በዐላት ከፖለቲካ አስተሳሰብ የጸዱ የአምልኮ በአላት ናቸው የሚለው ከሁሉ የበረታ እውነታ ነው፡፡ አንዳንዶች በእግዜር የክብር ቀን ቄሳርን ሆነው የግል ፍላጎትና ዓላማቸውን ያስፈጽማሉ፡፡ አንዳንዶች እድል አገኘን ብለው በሰላም መድረክ ፊት ጥላቻን ይነዛሉ፡፡ ይሄ ሀገርንም ሕዝብንም ወደ ነገ የማያራምድ ድርጊት ነው፡፡ ከቻልን ፍቅርን እንስበክና ከጥላቻ እንውጣ፡፡ ካልቻልን ዝም በማለት አስተዋጽኦ እናድርግ።

ምንም ማድረግ በማንችልበት ሰሞን ላይ ዝም በማለት ምንም ማድረግ እንችላለን፡፡ ባለማወቅ አስተዋጽኦ መስሎን የምናወራው፣ የምንናገረው አንዳንድ ነገር በምንም የማይጠፋ እሳት ሲያስነሳ እናያለን፡፡ ሀገራችንን ለኩሰው አልጠፋ ያለን እሳት የቆሰቆሱ እነሱ ዝም ማለት አቅቷቸው የዘባረቁ አፎች የወለዱት ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ትንሽ ነገር እንዲያስኮርፋቸው ሆነው በቆሙ ሕዝቦች መካከል ዝም ማለት ከመልካም አፍ በላይ ራሱን የቻለ በጎ አስተዋጽኦ ነው፡፡

ዝም ማለት አቅቶን በስሜት የምንተፋቸው ቃላቶች ናቸው በምንም የማይላላ ጥብቅ ቋጠሯችንን አላልተው ያራራቁን፡፡ መደማመጥና መነጋገር አቅቶን እዛና እዚህ ሆነን የተለዋወጥናቸው የይዋጣልን ቃላቶች ናቸው ከእርቅና ከተግባቦት አርቀው የዛሬዋን ኢትዮጵያና የዛሬውን እኛን የጸነሱት፡፡

አጋጣሚ እየፈለግን ጥላቻን ከመንዛት አጋጣሚን እየፈለጉ አንድነትን መስበክ ነው ኢትዮጵያን ቀና የሚያደርጋት፡፡ እድል ስናገኝ የማይሆን ከማውራት እድል ስናገኝ እርቅን ማስተጋባት ነው ታሪክ የሚያድሰው። እንደጥምቀት ባሉ የሰላም በዐላት ላይ የሚስተጋቡ በጎ መልዕክቶች ሀገር ከማጽናት አኳያ ፋይዳቸው የት የሌለ ነውና እንጠቀምባቸው፡፡

ከቻልን ክፉ ባለመናገርና በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ባለመሆን ለሀገራችን ውለታ እንዋል፡፡ ከቻልን አስታራቂና አዋዳጅ ቃላትን እንናገር፡፡ ከቻልን ስለፍቅር አፋችንን እንክፈት፡፡ ስለኢትዮጵያዊነት ድምጻችንን እናጉላ፡፡ ተከባብሮና ተቻችሎ ከሶስት ሺ ዘመን ለራቀ ዘመታት ስለኖረ ኢትዮጵያዊነት እንመስክር፡፡

ተዋልዶና ተጋምዶ በደምና በስጋ ስለተዋረሰ፣ ልዩነት ስለሌለው ጉራማይሌ መልካችን እንናገር። ተያይዞና ተደጋግፎ ከዛ ወደዚህ ስለመጣ ጥቁርነት እናውሳ። ስለለያዩን ጥቂት ነገሮች ሳይሆን ስላፋቀሩን ብዙ ነገሮቻችን ምስክርነት እንስጥ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታዩ ያሉ የአምልኮ ስርዐቶች መንፈሳዊ ዓላማቸውን እየሳቱ የተቃዋሚና የደጋፊነት አዝማሚያ እየተስተዋለባቸው ይገኛል። ይሄ አይነቱ አካሄድ ለማንም የማይጠቅም የደመቁ የአብሮነት መልኮቻችንን ከማደብዘዝ ባለፈ ክብር አይጨምሩልንም፡፡

‹ጥምቀት ሰላም ነው..ሰላምም ለጥምቀት ነው› የሚል እና ንጹህና ዓለማዊ መልክ የሌለው አምልኮ ነው ፈጣሪን በማክበር ተቀናቃኝ የሌለው የሚል ይሆናል። ለጥምቀት በክት ልብሳችን፣ የክት ሀሳባችንን ትተን በፍቅርና በአንድነት ፈጣሪን የምናመልክበት እንዲሆን ከወዲሁ መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ፡፡

ማህበራዊ

## ሀገርኛ

# የጎዳና ተዳዳሪዎችን በዘላቂነት የማቋቋም በጎ ተግባር

አንተነህ ቸሬ

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚከሰቱ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ከሚፈጥሯቸው ማኅበራዊ ቀውሶች መካከል አንዱ የጎዳና ተዳዳሪነት ነው፡፡ ይህ ችግር በኢትዮጵያም በሰፊው ተንሰራፍቶ የሚታይ ማኅበራዊ ቀውስ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በ11 ዋና ዋና ከተሞች ከ89ሺ በላይ ጎዳና ተዳዳሪዎች እንዳሉና ከእነዚህም ውስጥ ከ55ሺ በላይ የሚሆኑት በአዲስ አበባ ከተማ እንደሚገኙ ከአራት ዓመታት በፊት ይፋ የተደረገ የጥናት መረጃ ያሳያል፡፡

በችግሩ ምክንያት የሚፈጠሩ ቀውሶች ቤተሰብን፣ ሕብረተሰብንና ሀገርን ብዙ ዋጋ እያስከፈሉ ናቸው፡፡ ይህ አደገኛ ችግር ያሳሰባቸው በጎ አሳቢ ዜጎች፣ ችግሩ ከዚህ የበለጠ ቀውስ እንዳያስከትል በየጊዜው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ ቢስተዋልም፣ ችግሩን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች ግን ስር ነቀል ለውጦችን ማስመዝገብ አልቻሉም፡፡

የ«ቤተ-ሳይዳ የበጎ አድራጎት ድርጅት» መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ዓለምፀሐይ በቀለ በ1998 ዓ.ም በሐዋሳ ከተማ የጀመሩት ተግባርም ይህን ችግር የማቃለል ጥረት ማሳያ ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ወይዘሮ ዓለምፀሐይ በወቅቱ ሐዋሳ ገብርኤል አካባቢ ለጎዳና ሕይወት የተጋለጡ ሁለት ልጆችን ይመለከታሉ፤ በቻሉት አቅም ልጆቹን ለመርዳትም ይወስናሉ፡፡

«ስራው የተጀመረው ሁለት የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናትን በመርዳት ነበር፡፡ ሕፃናቱ ወላጆች ቢኖራቸውም ለጎዳና ሕይወት የተዳረጉ ናቸው፡፡ በወቅቱ ልጆቹን እየጎበኘሁ አንዳንድ ድጋፎችን ማድረግ ስጀምር ሌሎች ልጆችም ተጨመሩ፡፡ ምግብን ጨምሮ ሌሎች ድጋፎችን እናደርግላቸው ነበር፡፡ ሌሎች በጎ ፈቃደኞችም ለልጆቹ እገዛ ያደርጉ ነበር፡፡ በሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም ድጋፍ የሚደረግላቸው ልጆች ቁጥር 22 ደረሰ፤ ሕፃናቱ ድጋፍ የሚደረግላቸው በሚኖሩበት ስፍራ ላይ ነበር። ስለመልካም ስነ ምግባር ምንነት እናስተምራቸውም ነበር» በማለት ስለምግባረ ሰናይ ተግባራቸው አጀማመር ይገልጻሉ፡፡ በመቀጠልም ከበጎ ፈቃደኞች በተገኘ ድጋፍ ሕፃናቱ ትምህርት ቤት ገቡ፡፡

ወይዘሮ ዓለምፀሐይ እንደሚሉት፣ ለሕፃናቱ ከሚደረጉት ድጋፎች በተጨማሪ በዓላትን ምክንያት በማድረግ ቤተሰቦቻቸውም ድጋፍ ይደረግላቸው ነበር። በነሐሴ 1999 ዓ.ም ከደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ፈቃድ በማውጣት ስራቸውን አጠናክረው ገፉበት፡፡ ድጋፍ የሚደረግላቸው 22 ሕፃናትም ትምህርታቸውን ቀጠሉ፡፡

በመቀጠልም ድርጅቱ ስራውን ሰፋ አድርጎ ለመስራት በማሰብ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር መስራት ጀመረ፡፡ «ከትልልቅ መንግሥታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ጋር በትብብር የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ተቋማት ከፌዴራል መንግሥት የስራ ፈቃድ ማውጣት ይኖርባቸዋል ስለተባለ፣ በ2004 ዓ.ም ከሐዋሳ ወደ አዲስ አበባ መጥተን ‹ቤተ-ሳይዳ የሕፃናትና ወጣቶች መርጃ ማኅበር› በሚል ስም ከፌዴራል መንግሥት የበጎ አድራጎት ማኅበራት ኤጀንሲ ፈቃድ አወጣን» የሚሉት ወይዘሮ ዓለምፀሐይ፣ ከኤጀንሲው ያገኙት እውቅና ከሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድጅቶች ጋር በትብብር እንዲሰሩ ትልቅ እገዛ እንዳደረገላቸው ይገልፃሉ፡፡

ድርጅቱ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚያደርገው ትብብር ቀጥሎ፣ ትብብሩ ከእነዚህ ድርጅቶች መጠነኛ የገንዘብ ድጋፎችን እንዲያገኝ አስቻለው፡፡ በዚህም በሐዋሳ ከተማ ለተለያዩ ችግሮች ለተጋለጡ ሴቶችና ሕፃናት ልዩ ልዩ ድጋፎችን ማድረግ ችሏል፡፡

«ቤተ-ሳይዳ የበጎ አድራጎት ድርጅት» በአዲስ አበባ፣ ቱሉ ዲምቱ አካባቢ የሕፃናትና ሴቶች ማቆያ ማዕከል አለው፡፡ ለጎዳና ሕይወት ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ወደ ማዕከሉ ገብተው ልዩ ልዩ ድጋፎች ይደረግላቸዋል፡፡ ድርጅቱ ቀደም ሲል ድጋፍ የሚያደርገው ድጋፍ የሚደረግላቸው አካላት ወዳሉበት ቦታ በመሄድ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ድጋፍ ፈላጊዎቹ ወደ ድርጅቱ ቢሮ ሄደው አንዳንድ ድጋፎችን ያገኙም ነበር፤ በአሁኑ ወቅት ድጋፍ የሚደረገው ደግሞ በመጠለያ ውስጥ ነው፡፡

> **«ቤተ-ሳይዳ» የበጎ አድራጎት ድርጅት ለሕፃናት የምግብ፣ የትምህርትና የጤና ድጋፎችን ከማድረግ በተጨማሪ በመልካም ስነምግባር፣ በሴቶች ጥቃት፣ በጎዳና ሕይወት፣ በኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ በገቢ ማስገኛና በሌሎች ጾንሰ ሃሳቦች ላይ ያተኮሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችንና ስልጠናዎችንም ይሰጣል**

«ለጎዳና የተጋለጡ ሴቶችና ሕፃናት ቱሉ ዲምቱ አካባቢ ወደሚገኘው መጠለያ (ማቆያ) ገብተው ለአራት ወራት ያህል ድጋፍ ሲደረግላቸውና ስልጠናዎችን ሲወስዱ ቆይተው፣ ወደመጡባቸው አካባቢዎች ተመልሰዋል፡፡ በዚያም ቤት ተከራይተንላቸው ከኅብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉና እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ አሁን ደግሞ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ 29 ሴት ሕፃናትን ወደ መጠለያ አስገብተን ድጋፍ እያደረግንላቸው እንገኛለን፡፡ መጠለያ ውስጥ በሚቆዩባቸው ወራት የተለያዩ ድጋፎችን እናደርግላቸዋለን፤ ሙያዎችን ይማራሉ፡፡ ስለጎዳና ሕይወት አስከፊነት እና ስለገቢ ማስገኛ ስራዎች ግንዛቤ ካስጨበጥናቸው በኋላ ወደ ኅብረተሰቡ እንመልሳቸዋለን፡፡ ሕፃናቱም ወደ ኅብረተሰቡ ተመልሰው ትምህርት እንዲጀምሩ እናደርጋለን» በማለት ወይዘሮ ዓለምፀሐይ በመጠለያው ውስጥ ስለሚደረገው ድጋፍም ያብራራሉ፡፡

«ቤተ-ሳይዳ» የበጎ አድራጎት ድርጅት ለሕፃናት የምግብ፣ የትምህርትና የጤና ድጋፎችን ከማድረግ በተጨማሪ በመልካም ስነምግባር፣ በሴቶች ጥቃት፣ በጎዳና ሕይወት፣ በኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ በገቢ ማስገኛና በሌሎች ጽንሰ ሃሳቦች ላይ ያተኮሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችንና ስልጠናዎችንም ይሰጣል፡፡

ድርጅቱ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ባገኘው ድጋፍ ባለፈው ዓመት በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ኤፍራታና ግድም ወረዳ በግጭቶች ምክንያት ለተፈናቀሉ 200 ሴቶችና 250 ሕፃናት የምግብና የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል። ለ30 ሴቶች የገቢ ማስገኛ ስልጠናዎችን በመስጠት ፍየልና በግ ገዝቶ ሰጥቷል፡፡ ይህም ሴቶቹ ከዕለታዊ ድጋፍ ጠባቂነት ወጥተው በዘላቂነት እንዲቋቋሙና የኑሮ መሰረት እንዲኖራቸው እገዛ ያደርጋል፡፡

«ቤተ-ሳይዳ»የበጎ አድራጎት ድርጅት ከሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በትብብር የሚያከናውነው ፕሮጀክትም ሴቶችና ሕፃናት ከጎዳና ሕይወት እንዲላቀቁ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ «ዘንድሮ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የምንሰራው ስራ አለ፡፡ ይህም ለጎዳና ሕይወት የተጋለጡ ሴቶችንና ሕፃናትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ ከመንግሥት አካላት ጋር በትብብር መስራት ስራውን የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል ያግዛል» ይላሉ፡፡

«ቤተ-ሳይዳ» የበጎ አድራጎት ድርጅት እስካሁን ድረስ ከሁለት ሺ በላይ ለሚሆኑ ወገኖች ቋሚ ድጋፍ አድርጓል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የስነ ምግባር ትምህርት የተሰጣቸውና ቋሚ ባልሆነ መልኩ አልፎ አልፎ ድጋፍ ያገኙ ወገኖች ደግሞ ከ22ሺ በላይ ናቸው፡፡ ድርጅቱ ለስራው የሚያስፈልገውን ገንዘብ የሚያገኘው ከበጎ አድራጊዎች ከሚሰበሰቡ ድጋፎች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ከሚደረጉ ትብብሮች እንዲሁም ከፕሮጀክቶች ከሚገኙ ድጋፎች ነው፡፡

«ቤተ-ሳይዳ» የበጎ አድራጎት ድርጅት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ያከናወናቸው ተግባራት የበርካቶችን ሕይወት የለወጡና ለማኅበራዊ መረጋጋትም ትልቅ አዎንታዊ አስተዋፅዖዎችን ያበረከቱ እንደሆኑ ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ያብራራሉ፡፡

«ድርጅቱ እገዛ ያደረገላቸው ሕፃናት ተምረው ስራ ይዘዋል፡፡ አንዳንዶቹ በድርጅቱ ውስጥ ሶሻል ወርከርና የሂሳብ ሰራተኛ ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በድርጅቱ ድጋፍ አድገውና ተምረው ዛሬ በሐዋሳ ከተማ በተለያዩ የሙያ መስኮች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ብዙ ወጣቶች አሉ፡፡ ‹ቤተ-ሳይዳ› ድጋፍ ያደረገላቸው ልጆች አዲስ አበባ ላይም የተለያዩ ስራዎችን እየሰሩ ራሳቸውን እየቻሉ ነው፡፡ ድጋፍ ያደረግንላቸው ሴቶችም በተለያዩ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ኑሯቸውን እየመሩ ይገኛሉ፡፡ ልብስ በመስፋት፣ በንግድ ስራ ውጤታማ የሆኑ ሴቶች አሉ፡፡ ከሐዋሳ ከተማ ወጣ ባሉ አካባቢዎች ደግሞ ፍየልና በግ እንዲያረቡ የሰጠናቸው ሴቶች በርትተው ሰርተው ጥሩ ውጤቶችን አሳይተውናል» በማለት የድርጅቱ ምግባረ ሰናይ ተግባራት ስላስገኟቸው ውጤቶች ያስረዳሉ፡፡

«ስራውን የጀመርነው ሰው እንዲያውቀልንና እንዲያወራልን ሳይሆን የተቸገሩ ሰዎችን ለመርዳት ብቻ ነው» የሚሉት ወይዘሮ ዓለምፀሐይ፣ ይህ እምነታቸው ለብዙ ዓመታት ከመንግሥት ተቋማት ጋር ጠንካራ የሚባል ትስስር ሳይፈጥሩ እንዲቆዩ እንዳደረጋቸው ይናገራሉ፡፡ «ለብዙ ዓመታት መንግሥት ሳይደግፈን በሐዋሳ ከተማ በቤት ለቤት አገልግሎት ብዙ ስራዎችን ሰርተናል፡፡ መንግሥት ያወቀን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው። ራሳችንን አለማስተዋወቃችን ገንዘብ ለማግኘትም ሆነ ከሌሎች ተቋማት ጋር ትብብር ለመፍጠር ሳያስችለን ቆይቷል፡፡ አሁን ከሴቶችና ሕፃናት እንዲሁም ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ተቋማት ጋር በጋራ እንሰራለን፡፡ የመንግሥት ተቋማት ጥሩ ድጋፍ ያደርጋሉ» በማለት ከመንግሥት አካላት ጋር በትብብር መስራት ስራውን አስፋቶና የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግ ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ስራውን ሲጀምሩ በሐዋሳ የራሳቸውን መኖሪያ ግቢ ለበጎ አድራጎት ስራው ቢሮ አድርገው ይጠቀሙበት እንደነበር ያስታውሳሉ። «የሰው መብላት፣ መጠጣትና መደሰት ለእኔ ትልቁ ደስታዬ ነው፡፡ ባለቤቴም በጣም ጥሩ ሰው ስለሆነ ለስራው መሳካት እገዛ ያደርግ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ያለው የቤት ኪራይ ግን በጣም ውድ ነው፡፡ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለጎዳና ተዳዳሪዎች ያለው ምልከታም አወንታዊ ባለመሆኑ ቤት ማግኘት ትልቅ ፈተና ነው» በማለት የቤት ኪራይ በስራቸው ላይ መሰናክል የፈጠረ ፈተና እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

ዳዊት ዳና በ«ቤተ-ሳይዳ» ድጋፍ ተምሮ ሹፌርና የኤሌክትሪክ ጥገና ባለሙያ ለመሆን የበቃ ወጣት ነው፡፡ «በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ነበርን። የምንመገበውና የምንለብሰው አልነበረንም። ወይዘሮ ዓለምፀሐይ አግኝታን ድጋፍ ስታደርግልን የሕይወታችን አቅጣጫ ተቀየረ፡፡ የትምህርት ቁሳቁስ፣ አልባሳትና ሌሎች ድጋፎች ይደረጉልን ነበር፡፡ ትምህርታችንን የተማርነው በ‹ቤተ-ሳይዳ› ድጋፍ ነው። ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ‹የሚያስፈልጋችሁን ነገር ሁሉ ጠይቁኝ› ትለን ነበር፤ እንደልጆቿ ትንከባከበናለች። የ‹ቤተ-ሳይዳ›ን ውለታ ስናገር ስሜቴን መቆጣጠር ይከብደኛል፤ ውለታቸውን እንዴት አድርገን እንደምንከፍል አላውቅም» በማለት ስለቀድሞ ሕይወቱና «ቤተ-ሳይዳ» የበጎ አድራጎት ድርጅት ስላደረገለት ድጋፍ ያስታውሳል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላም የ«ቤተ-ሳይዳ» ድጋፍ ያልተለየው ዳዊት፣ በሐዋሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በአውቶ ኤሌክትሪክ የትምህርት መስክ ተመርቆ በሹፌርነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ እናቱንና ታናሽ ወንድሙን እያገዘ ይገኛል፡፡ ከእርሱ ጋር በ«ቤተ-ሳይዳ» ድጋፍ ይደረግላቸው የነበሩ ጓደኞቹም በተለያዩ ሙያዎች ላይ ተሰማርተው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን እየደገፉ እንደሚገኝ ይገልፃል፡፡

ቸርነት ዓለማየሁ ሌላው የ«ቤተ-ሳይዳ» ፍሬ ነው፡ ወይዘሮ ዓለምፀሐይን ከማወቁ በፊት የጎዳና ተዳዳሪ እንደነበር የሚናገረው ቸርነት፣ ምግብና አልባሳትን ጨምሮ ሁሉንም ድጋፍ የሚያደርግላቸው «ቤተ-ሳይዳ» እንደነበር ይገልፃል፡፡ ቸርነት ትምህርትን ‹ሀ› ብሎ የጀመረውና እስከ ሙያና ቴክኒክ ትምህርት ቤት ድረስ ዘልቆ ለምርቃት የበቃው በ«ቤተ-ሳይዳ» ድጋፍ ነው፡፡ «ምን እንደምሆን አላውቅም ነበር፡፡ ወላጆቼ ቢወልዱኝም ለዚህ ደረጃ ያበቃችኝ ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ናት፡፡ ‹ቤተ-ሳይዳ› ለእኛ ብዙ ዋጋ ከፍሏል» ይላል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሹፌርነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው ቸርነት፣ ትዳር መስርቶ የአንዲት ልጅ አባት ለመሆን በቅቷል፡፡

«ቤተ-ሳይዳ የበጎ አድራጎት ማኅበር ሰዎች፣ በተለይ ወጣቶች፣ ድጋፍ ተደርጎላቸው ስራ እንዲሰሩ ማድረግ እንጂ ተረጂ ሆነው እንዲቀጥሉ አይፈልግም» የሚሉት ወይዘሮ ዓለምፀሐይ፣ ድርጅቱ የወደፊት እቅድም በዚሁ መርህ የተቃኘ እንደሆነ ይገልፃሉ። «መንግሥት ቦታ መስጠትን ጨምሮ ሌሎች ድጋፎችን ካደረገልን፣ ለጎዳና ሕይወት የተጋለጡ ሕፃናት በዘላቂነት እንዲቋቋሙና ከችግሩ እንዲወጡ የመስራት ትልቅ እቅድ አለን፡፡ ቦታ ከተሰጠን ብዙ ልጆችን መርዳት እንችላለን፡፡ ብዙ ሴቶች በየመንገዱ ወድቀዋል፤ እነዚህ ሴቶች ትንሽ ድጋፍ ከተደረገላቸው ግን ራሳቸውን መቀየርና ወደተሻለ የሕይወት መስመር መግባት ይችላሉ፡፡ ዋናው ዓላማችንና ፍላጎታችን የተቸገሩ ወገኖችን በዘላቂነት ማቋቋም ነው» በማለት ስለድርጅቱ እቅድ ይገልፃሉ፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ወጣቶች ከከተራ እስከ ጥምቀት

**አስመረት ብስራት**



ከተራ "ከተረ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም "ውሃ መከበብ" ወይም "መገደብ"ማለት ነው። የከተራ በዓል ከጥምቀት በዓል አንድ ቀን ቀድሞ ነው የሚከበረው። የጥምቀት ዋዜማ ታቦተ-ሕጉ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ውሃ ባለበት አካባቢ ስለሚያድር የየአጥቢያው የእምነቱ ተከታይ በአንድ ላይ በወንዝ ዳር ወይም በምንጭ አካባቢ ድንኳን ይተከላል፤ የወንዝ ወይም የምንጭ ውሃም ይገደባል፤ ይከተራል። ይህ በጥምቀት ዋዜማ የሚደረገው ውሃውን የመከተርና የመገደብ ስርዓትም "ከተራ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

የታሪኩ መነሻ መዝሙር 113 ቁጥር አምስት ላይ በመጽሃፍ ቅዱስ የተጻፈው ነው፡፡ "እየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ መሃል ላይ ሲቆም ባሕር ባሕር አይታ ሸሸች የሚለውን ቃል መነሻ በማድረግ ነው ይህ ክንውን የሚፈጸመው።

በዚህ መነሻነት ታቦታቱ ከየማደሪያቸው ወጥተው በውሃ ዳር በተዘጋጀ ቦታ ማክበር ከጀመሩ ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ ማስቆጠራቸውንም በከተራ ዙሪያ የተጻፉ ታሪኮች ያስረዳሉ።

የተጠራቀመው ውሃ በማግሥቱ ጥር 11 ቀን የጥምቀት በዓል ሲከበር የሕዝቡ መጠመቂያ ይሆናል። ከተራ በተለያዩ አካባቢዎች በተለይ በአክሱም የንግሥት ሳባ መዋኛ (ማይ ሹም)፣ በጎንደር የአፄ ፋሲል መዋኛ፣ በላስታ የላሊበላ መዋኛ፣ በሸዋ የአፄ ዘርዓያዕቆብ ፍርድ መስጫ አደባባይ፣ በአዲስ አበባ ደግሞ ጃንሆይ ሜዳ (ጃንሜዳ) በደማቅ ስነ-ስርዓት ይከበራል።

ከጥምቀት ዋዜማ ማለትም በየዓመቱ ጥር ፲(10) ቀን ለሕዝቡ መጠመቂያ እንዲኾን ምዕመናን ውኃውን በመከተር (በመገደብ) ስለሚውሉ ዕለቱ ከተራ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ውኃው የሚከተረው በማግሥቱ ጥር ፲፩(11) ቀን የጥምቀት በዓል ስለሚከበር ነው፡፡ ይህ ውኃ የሚከተርበት ሥፍራም “ባሕረ ጥምቀት” ወይንም “የታቦት ማደሪያ” ተብሎ ይጠራል፡፡

ሌላው የከተራ ዕለት ካህናቱ ታቦተ ሕጉን በራሳቸው ላይ አክብረው ወደ ባሕረ ጥምቀት መሄዳቸው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ መሄዱን ለመዘከር ነው፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ባሕረ ጥምቀት ለመሄድ ሲወጣ “ወረደ ወልድ እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት፡፡” የሚለው የሚዘመረውም ይኸንን እውነት ለመግለጽ ነው፡፡

በገጠሪቱ ኢትዮጵያም እንዲሁ ጥምቀት እጅግ በሚያስደስት መልኩ ነው የሚከበረው። በገጠር በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ጥምቀት የሚከበረው የከተራ ዕለት ታቦቱ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ዳገትና ቁልቁለት በበዛበት መንገድ ወደ ወንዝ ያመራል። ወንዝ ከደረሰ በኋላም ቀድሞ በወጣቶች እና በአገር ሽማግሌዎች በተተከለው የታቦቱ ማረፊያ ድንኳን ውስጥ እንደሚገባ እና ሌሊቱንም ካህናት እና ዲያቆናት ልዩ ልዩ ያሬዳዊ ዜማዎችን ሲያዜሙ ያድራሉ።

የአካባቢው ምዕመናን ድግስ ደግሰው ዝክር የሚያደርጉ ሲሆን፣ ማህሌት፣ ኪዳን እና ቅዳሴም በሌሊቱ መርሀ ግብር ይከወናሉ። በነጋ ጊዜም ከአራቱ ወንጌላውያን ስለ ክርስቶስ መጠመቅ ምንባብ ተነቦ ካለቀ በኋላ፣ ጥምቀተ ባህሩ ተባርኮ ካህናቱ ማጥመቅ ይጀምራሉ።

በተጨማሪም በጉዞ ላይ “እግዚኡ መርሐ፣ ሆረ እየሱስ፣ መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል” የሚሉትና ሌሎች መዝሙራት ይዘመራሉ፡፡ በኢትዮጵያ በተለይም በጎንደር በባቱና በአዲስ አበባ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ከተራና ጥምቀት በዓላት በዓደባባይ በድምቀት ይከበራሉ። በርካታ ቱሪስቶችም ዕለቶቹን ምክንያት አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ።

በእለቱ ሁሉም ያለውን ፃእዳውን ለብሶ ወደ መጠመቂያው ቦታ ይሄዳል። ያኔ መንፈሳዊ ስርዓቱ ተፈፅሞ ፀበልን ለመጠመቅ የሚደረገው መራኮት በራሱ ትልቅ ስሜትን የሚፈጥር ነው። ሰው የፀበሉ ቅንጣት ፊቱ ላይ ሲያርፍ የሚሰማው ደስታ እልልታው ጭብጨባው ረክቶ ወደየ ዝማሬው ይቀላቀላል።

" እኔስ የታቦት ስራ አለብኝ፤ እኛም እንዳንተው ስራ አለብን..." ተብሎ የተጀመረው ወጣቶች ቀድመው አካባቢን በማፅዳት በማሸብረቅ የጀመረውን ስራ ታቦታተ ሕጉ ከመንበራቸው ወጥተው ማደሪያቸው እስኪደርሱ ምንጣፍ በማንጠፍ፤ በመጥረግ፤ አካባቢውን ፀጥታ በማስከበር፤ በዝማሬ አድምቀው የሸኙትን መልሰው ለመቀበል ከፀበሉ ሰዓት ጀምሮ ዳግም ምንጣፎቹን በመሸከም ላባቸወን ሲያንጠፈጥፉ የሚውሉበት በዓል ነው በአለ ጥምቀት።

ከእናቶች ደርበብ ያለ የዝማሬ ድምፅ የሕፃናት የመለእክትን ዝማሬ የመሰሉ የመዝሙር ድምፆች፤ የወጣቶች ሽብሸቦና ጭብጨባ ይህ ሁሉ የጥምቀቱ ድምቀት ነው።

በከተራና በጥምቀት ወጣቶች ያሸበርቃሉ። የበዓሉ ድምቀት ይሆናሉ፡፡ ይህ ወቅት አየሩ ተስማሚ፤ አካባቢው ሁሉ ማራኪ ስለሚሆን የሚታየው ሁሉ ይወደዳል፤ የፍቅር ስሜት ያጭራል። የወጣቶችም አይንና ልብም ለፍቅር ይዘጋጃል፤ መፋቀር፤ መከጃጀል፤ መተጫጨት ብሎም መጋባት ከከተራ እስከ ጥምቀት ብሎም እስከ ቃና ዘገሊላ እና አስተሪዮ ማርያም ድረስ ባሉ በዓላት የተለመደ የጥር ወር ልዩ መገለጫ ነው፡፡

ከከተራ እስከ ጥምቀት ባሉት ቀናት ሴቶች አሸብርቀው አደባባይ ይገኛሉ፡፡ ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እንደሚባለው የክት ልብሳቸውን ለብሰው ጌጣጌጦችን ጨምረው አምረውና ደምቀው ከአደባባይ ይሰየማሉ። በዚህ ወቅት እንኳን ያላገባ ብላቴና ይቅርና በእድሜ ለገፉት ጎልማሳና ሽማግሌ ጭምር የኮረዳዎቹ ውበት ልብ የሚያርድ ነው። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ደግሞ ሎሚ መወራወርና መተጫጨት የቆየ ባህል ነው፡፡

በከተማ|ም ጓደኛሞች ተቀጣጥረው የሚገናኙበት፤ አንድ አይነት ልብሳቸውን ለማሳየት የሚወጡበት፤ ፍቅረኛሞች ያለማንም ከልካይ አብረው የሚውሉበት ቀንም ነው ከተራና ጥምቀት። ወጣቶች በተለያየ መልክ የሚያከብሩትን በአለ ከተራና ጥምቀት ከዝማሬው ጀምሮ እስከ ሀርሞኒካው ጭፈራ፤ ከሀርሞኒካው ዳንስ የባህላዊ ዘፈኖች ድምር ሁሉም ውብ ድምቀቶች ናቸው።

በትንፋሽ የሚነፋው ሀርሞኒካ በአብዛኛው አፍላ ወጣቶች የሚሳተፉበት የጭፈራ አይነት ነው። ሀርሞኒካውን ከሚነፋው ልጅ ሌላ በፉጨትና በጭብጨባ በሚያጅቡት ወጣቶች ይበልጥ ይደምቃል። ደናሾቹ ወንዶችና ሴት ወጣቶቸ ሲሆኑ የራሱ አጨፋፈር ስልት ባለውና የሀርሞኒካውን ድምፅ ተከትሎ በሚደረገው ውዝዋዜ በርካታ ወጣቶች ደስታቸውን የሚገልፁበት የመዝናናት የመደሰት ቀናት ናቸው በአለ ከተራና ጥምቀት ለወጣቱ።

ወንዶች እና ሴቶችን በነጠላ ተሸፍነው ከዚያም ውስጥ ሆነው ይጨፍራሉ። ሌላ የተለየ ነገር ምን እንደሚያደርጉም አይታወቅም። የደከሙት ሲወጡ የሚተኩ ሌሎች ሴቶችም ወንዶችም ወጣቶች ይኖራሉ። ሀርሞኒካ ማለት እንኳን ለዘንድሮው በዓል በሰላም አደረሰን የሚለውን ለመግለጽ ወጣቶች ያደርጉት የነበረ ጭፈራ አይነት መሆኑንም ብዙሀኑ ይስማሙበታል።

በአብዛኛው በአለ ጥምቀት ሀይማኖታዊ ስርአትን የተከተለ በመሆኑ ቀሳውስቱም ይሁኑ ሌሎች የሀይማኖቱ አስተማሪዎች በሚያደርጉት ጫና በዓሉ ሀይማኖታዊ ይዘት ብቻ እንዲኖረው እየተደረገ በመሆኑ የሀርሞኒካ ዝነኝነት አሁን ላይ ተቀዛቅዟል።

በገጠር ጥምቀቱ ተጠምቆ ታቦቱ ወጥቶ ድንኳን እስከሚነቀል ድረስ ባለው ቦታ እዛው በታቦት ማደሪያ አካባቢ ወጣቶች የገና ጨዋታ ይጫወታሉ፣ አዳዲስ ልብስ የለበሱ ልጃገረዶች ዘፈንና ጭፈራ ያካሂዳሉ።

በዚህም ከሚጨፍሩ ልጃገረዶች መካከል አንዱ ጉብል ዐይቶ የወደዳትን ሎሚ ይወረውርባታል፤ አልያም አብራው እንድትጨፍር ይጋብዛታል። በገጠር በዚህ መንገድ ተዋውቀው ትዳር የመሠረቱ ብዙ ወጣቶች አሉ።

በድሮው ዘመን አንድ ወንድ አንዲት የሚወዳትን ሴት እንደሚፈልጋት ለማሳወቅ ጥምቀት እስከሚመጣ ዓመት ሙሉ ይጠብቅ እንደነበር ይነገራል። ከቤት ስለማትወጣ ሌላ ቦታ የማያገኛት ከመሆኑም ሌላ፣ ቢያገኛት እንኳን እንደሚፈልጋት መናገር አይችልም ነበር። በዚህም እንደ ጥምቀት ያሉ የአደባባይ በዓላትን መጠበቅ ይኖርበታል።

ወጣቱ መንፈሳዊ ግልጋሎቱ፤ በባህላዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዝማሬ መሳተፉ፤ የአገልግሎት ስራ ላይ መሳተፉ ልቡ የከጀላትን በበአሉ ላይ ማግኘቱ የገጠሩም የከተማውም አከባበር አንድ አይነት መሆኑን ልብ ይለዋል።

ደራሲ መላኩ አላምረው ‹ነፍጠኛ ስንኞች› በተሰኘ የግጥም ስብስብ መጽሐፉ (ገጽ 54) በጥምቀት በዓል ወቅት ድሮ የነበረውን እና አሁን የሚስተዋለውን በማነጻጸር በሚከተሉት ስንኞች ቋጥሮ አስቀምጦታል፤

ባህልን አክብሮ፣ ከእንስት ርቆ፣
በዓመት አንድ ጊዜ ጥምቀትን ጠብቆ፣
ከኮረዳ መሀል ከውብም ውብ መርጦ፣
ልቡ እንደወደዳት በውል አረጋግጦ፣
ሎሚ በመወርወር የሴት ደረት መትቶ፣
ውቢቷ ኮረዳም ደረቷ ሲመታ፣ ልቧ ተደስቶ፣
‘ሚኖርበት ዘመን፣
ሰው ከሰው ተጫጭቶ፣
ሰው ከሰው ተጋብቶ፣
ድሮ ቀረ ድሮ...
ሰው ከውጭ ተምሮ ባህል ተቀይሮ፣
ሎሚም ዋጋው ንሮ አልሆነም ዘንድሮ ...!
ያሁኑ ጎረምሳ፣
ኮረዳ ለመቅረብ፣ ጥምቀት አይጠብቀም፣
ያው ዓመቱን ሙሉ ከሴት ጥግ አይርቅም።
የኮረዳም ደረት፣
ለጥምቀቱ ሎሚ አሻፈረኝ አለ፣

ቀድሞ ተገላልጦ አደባባይ ዋለ። በማለት ወደ ባህላችንና ወደ ቀልባችን እንድንመለስ ሸንቆጥ የሚያደርግ ስንኝ ቋጥሯል፡፡

በአለ ጥምቀት በዓለም የትምህርት፣ ሳይንስና ባሕል ድርጅት (ዩኒስኮ) የተመዘገበ የማይዳሰስ ቅርስ በመሆኑም በየዓመቱ በርካታ የውጪ አገር ቱሪስቶችን ወደ አገር ውስጥ የሚስብ ነው።

በማህበራዊ ዘርፍም እንደሚስተዋለው ወጣቶች በጋራ ሆነው ከከተራ በፊት ጀምሮ አደባባዮችን ሲያስጌጡ እና መንግዶችን ሲያስውቡ ይታያል። የበዓሉ ዕለትም በርካቶች ተሰባስበው በጋራ የሚያከብሩት በመሆኑ አንድነት እና ፍቅርን የሚያጠናክር ታላቅ በዓል መሆኑ ይታያል።

የእየሱስ ክርስቶስን መጠመቅ መሠረት በማድረግ የጥምቀት በዓልን ከኢትዮጵያ በተጨማሪ፣ ኤርትራ፣ ሩስያ፣ ጆርዳን እና ዩክሬንም በዓሉን በድምቀት ከሚያከብሩ አገራት ውስጥ ይገኙበታል።

# የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ተስፋ ሰጪ የማዕድን ልማት

ወርቅነሽ ደምሰው

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በበርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች የበለጸገ ነው:: በክልሉ ከፍተኛ ክምችት ያለው የማዕድናት ሀብት ይገኛል:: እንደ ወርቅ ያሉ የከበሩ ማዕድናት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለኮንስትራክሽን እና ለመሳሳሉት በግብአትነት ሊውሉ የሚችሉ እንደ ድንጋይ ከሰል ያሉ በርካታ ማዕድናት በስፋት አሉት:: ክልሉ በአሁኑ ወቅት በተለይ በድንጋይ ከሰል ማአድን ባለቤትነቱ ብቻ ሳይሆን በምርቱም መታወቅ ችሏል::

ከክልሉ የተገኘ መረጃ እንዳመለከተው፤ የክልሉን ማዕድናት በጥናት ለመለየት በተከናወነ ተግባር በርካታ ማእድናት መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፤ በአንጻሩ ገና ያልተለዩ ማእድናትም አሉ:: በጥናት የተለዩትን ማዕድናት በማልማት ረገድ ተስፋ ሰጪ ሥራዎች ተጀምረዋል::

የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ ምክትል ዳይሬክተርና የማዕድን ዘርፍ ኃላፊ አቶ መንገሻ መዳልቾ ክልሉ እንደ ውሃ አካላት፣ ማዕድን ሀብት እና ደን ሀብት ባሉት የተፈጥሮ ሀብቶች የበለጸገ መሆኑን ይገልጻሉ። በክልሉ በርካታ የማእድን ሀብቶች ቢኖሩም አልምቶ ከመጠቀም አንጻር ቀደም ሲል ክልሉ ውስንነቶች ነበሩበት የሚሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር እምብዛም እንዳልተሰራም ይገልጻሉ:: የማዕድን ዘርፍ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት በመንግስት ታምኖበት ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ተከትሎ በክልሉ የማእድን ሀብቶች ላይ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙም ይናገራሉ::

## ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ ማዕድናት

በክልሉ የማዕድን ዘርፍ እየተከናወኑ ካሉ ተግባሮች መካከል ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚሆኑ ማእድናት ልማት በሰፊው እየተሰራበት ይገኛል:: ለኢንዱስትሪ ኃይል ማመንጫነትና ለመሳሰሉት ግብዓት ሊውል በሚችለው የድንጋይ ከሰል ልማት ላይ በስፋት እየተሰራበት ነው:: የድንጋይ ከሰል ጥራትን መጨመር የሚያስችል ፕሮሰሲንግ ማሽን በዳውሮ ዞን የተከላ ሥራው እየተጠናቀቀ ይገኛል። ሌሎች የድንጋይ ከሰልን በሰፊው ለማምረት የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችና ፍላጎቶችም አሉ::

ለሴራሚክ ማምረት ስራ ግብዓት የሚውሉ ካዮሊን፣ ግራናይት፣ እምነበረድ፣ የኖራ ድንጋይ እና የመሳሳሉት ማዕድናት በክልሉ በስፋት ይገኛሉ:: እነዚህን ማዕድናት ለማልማት አልሚዎች ማዕድኑን በጥናት በመለየት ወደ ምርት ፈቃድ ደረጃ እየተሸጋገሩ ይገኛሉ::

ይህም አሁን የማዕድን ዘርፉ ልማት ተጠናክሮ መቀጠሉን ተከትሎ ለውጥ አምጥቷል የሚባል ባይሆንም፣ ተስፋ ሰጪ ነገሮች ስለመኖራቸው ግን አመላካች ነው:: ለሴራሚክ ማምረት ስራ ግብዓትነት የሚውሉ ማዕድናት ሰፊ ክምችት መኖሩ ወደፊት በክልሉ ፋብሪካዎችን የመቋቋም ተስፋ እንዳለ ያሳያል::

ሌላኛው የኖራ ድንጋይ ሲሆን፣ ይህም ከ50 ዓመትና ከዚያ በላይ ሊመረት የሚችል ክምችት መኖሩ ከተረጋገጠ በክልሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን የማቋቋም እድል ይፈጥራል:: አሁን የእነዚህን ማዕድናት ክምችት በደንብ ለማወቅ ጥናቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፤ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች መኖራቸውም ለማዕድን ዘርፉ ተስፋ የሚሰጥ እድል መኖሩን እንደሚያመላክት ነው ምክትል ዳይሬክተሩ የጠቆሙት::

## የኮንስትራክሽን ማዕድናት

ክልሉ ለኮንስትራክሽን ዘርፉ ሊውሉ የሚችሉ ማዕድናት መገኛም ነው:: እምነ በረድ፣ ግራናይት፣ የኖራ ድንጋይ (ለሕንጻና ለግርግዳ ምንጣፍ የሚውል በመሆኑ) እና ሌሎች ማእድናትን የመለየት ስራ እየተከናወነ ነው::

## ብረትና ብረትነክ ማዕድናት

በክልሉ ከሚገኙት ማእድናት መካከል ብረትና ብረትነክ ማዕድናት ይጠቀሳሉ:: በአዋጁ መሠረት ብረትና ብረትነክ ማዕድናት ፈቃድ የሚሰጠው በማዕድን ሚኒስቴር አማካኝነት ነው:: በመሆኑም በምርመራ ሥራ ፈቃድ ያገኙ ባለሀብቶች በክልሉ በዳውሮ ዞን፣ በኮንታ እና በከፋ ኮሪደሮች ላይ ፈቃድ አግኝተው በእነዚህ ማእድናት ላይ ጥናት እያደረጉ ይገኛሉ:: ከዚህ በተጨማሪ ብረትና ብረትነክ ማዕድናትን በባሕላዊ መንገድ ለሚያወጡ የአካባቢው ሰዎች ማእድናቱን የማውጣት ፈቃድ ተሰጥቷቸው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ::

## የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት

የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትም በክልሉ ይገኛሉ። ከከበሩ ማዕድናት ውስጥ አንዱ የወርቅ ማእድን ሲሆን፣ በክልሉ በወርቅ የማምረት ሂደት የአፈጻጸም ውስንነት ቢኖርም ወርቅ የማምረት ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው:: ወርቅ ለማምረት በማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ የተሰጣቸው በምርመራ ላይ የሚገኙም ኩባንያዎች አሉ። በክልሉ ፈቃድ የተሰጣቸው ባሕላዊና አነስተኛ የወርቅ አምራቾች ደግሞ በማምረት እንቅስቃሴ ላይ ናቸው::

የወርቅ ማውጣቱ ስራ በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶት ከወትሮ በተለየ መልኩ ድጋፍና ክትትል እየተደረገበት መሆኑን ተከትሎ ወርቅ የማምረት ሂደቱ አሁን በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ምክትል ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል::

የጌጣጌጥ ማዕድናትም ከከበሩ ማዕድናት መካከል የሚመደቡ ናቸው:: ክልሉ የተለያየ ቀለም ያላቸው የአጌት፣ ኦፓል እና የመሳሳሉት ማዕድናት መገኛም ነው፤ በቤንች ሸኮ ዞን አካባቢ አንድ አልሚ የኦፓል ማዕድን ማልማት ፈቃድ አውጥቶ ወደ ምርት ሥራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ነው::

## በማዕድን ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች

በምዕራብ ኦሞ ዞን በኮንስትራክሽን ማዕድናት ላይ ሁለት ባለከፍተኛ ፈቃድ አልሚዎች ፈቃድ ወስደው በእምነበረድ ልማት ላይ ተሰማርተዋል:: በዳውሮ ዞን ሁለት አምራቾች በግራናይትና በኖራ ድንጋይ ልማት ላይ የተሰማሩ ሲሆን፤ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውለው የካዮሊን ማዕድንን ለማምረት አንድ ባለሀብት ፈቃድ ወስዷል::

‹‹የድንጋይ ከሰል ማዕድን በማምረት ሂደት 18 የሚሆኑ አምራቾች ተሰማርተዋል›› ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፣ ‹‹አሁን ብዙዎቹ በቅኝትና በምርመራ ሂደት ላይ ይገኛሉ›› ብለዋል:: በማዕድን ቅኝትና ምርመራ ስራ ለመሰማራት 178 ያህል ፍላጎቶች እንዳሉም ጠቅሰው፣ በክልሉ ያለው የማዕድን ሀብት ውስን እንደመሆኑ በዘርፉ ተሰማርተው የነበሩትን አምራቾች በአግባቡ ተቆጣጥሮ ወደ ሥራ ለማስገባት ስለተፈለገ አዲስ ፈቃዶችን የመስጠቱ ሥራ መታገዱን ምክትል ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል::

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዝናባማ አካባቢ እንደሆነና ከባለፈው ዓመት የካቲት ወር እስከ ኅዳር ወር ድረስ በክልሉ ዝናብ ይጥል እንደነበር አስታውሰው፤ አምራቾች አሁን ፈቃዳቸውን አድሰው ወደ ምርት ሥራ ለመግባት እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑንም አመላክተዋል። በበጀት ዓመቱ ያለው የምርት አፈፃፀም በጣም ውስንና ማምረት ከተፈለገው አቅም በታች መሆኑንም አስታውቀዋል::

## የገበያ ትስስር

በአንዳንድ አምራቾች በኩል የሚቀርቡ የገበያ ትስስር ችግሮች እንዳሉም ምክትል ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል። እነዚህም ከጥራት ጋር ተያይዘው የሚነሱት ችግሮች መሆናቸውን ይገልጻሉ፤ በክረምት ምክንያት ምርቶችን ከቦታ ወደ ቦታ ለማንቀሳቀስ ከመንገድ ጋር ተያይዞ መስተጓጎል እንደሚታይ ጠቅሰው፤ አምራቾች በተፈጠረው የገበያ ትስስር መሠረት ምርቶችን በፍጥነት ማቅረብ እንዳልቻሉ ተናግረዋል:: ምርቱን የሚፈልጉት ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ምርቶቹን ከሌላ ቦታ በማምጣት እየተጠቀሙ መሆናቸውን ተከትሎ የአካባቢው አምራቾች በድጋሚ የገበያ ትስስር ለማግኘት እንደሚቸገሩ አመልክተዋል::

## የሥራ እድል ፈጠራ

በማዕድን ዘርፉ የሥራ እድል ፈጠራን በተመለከተ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ውስጥ ለሦስት ሺ607 ሥራ አጥ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ ለሁለት ሺ 711 ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል::

## ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት 15 ኪሎግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ መቻሉን ጠቅሰው፣ የክልሉ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ በሰራው ሥራ አሁን በወር 22 ኪሎግራም የወርቅ ምርት ወደ ብሔራዊ ባንክ ማስገባት ተችሏል ብለዋል:: የወርቅ ወርሃዊ ምርት መጠን እየጨመረ መምጣቱን ጠቅሰው፣ ቀጣይነቱ ላይ ግን ስጋቱ እንዳላቸውም ምክትል ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል። ‹‹ጥብቅ ቁጥጥር ሲደረግ የተወሰነ መሻሻሎችን ያሳያል፤ ቁጥጥሩ ሲላላ ደግሞ ምርቱ በዚያው ልክ ያሽቆለቁላል›› ይላሉ::

የወርቅ ሕገወጥ ዝውውር በወርቅ ምርት ላይ የተጋረጠ ከባድ ፈተና መሆኑን ጠቅሰው፣ በኮንትሮባንድ የመሸጥና ወደ ጋምቤላ ክልል ይዞ የመውጣት ችግሮች ይስተዋላሉ ብለዋል:: በዚህ የተነሳ አነስተኛ የወርቅ አምራቾች ማህበራት የፈረሱበት ሁኔታ እንዳለም ገልጸዋል:: ይህን ሕገወጥ የወርቅ ዝውውር ለመቆጣጠር ሲሰራ መቆየቱን ገልጸው፣ የወርቅ ማምረቻ ቦታው ወደ ድንበር አካባቢ ስለሆነ ለክትትል አመቺ አይደለም ይላሉ፤ ክትትሉ በዘላቂነት እንዳልቀጠለም ጠቅሰው፣ ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ከክልሉ ከጸጥታ መዋቅር ጋር እየተሰራ ያለው ሥራ ይጠናከራል ሲሉም አስታውቀዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በ2016 በጀት ዓመት 400 ኪሎግራም ወርቅ ለማምረት የታቀደ ሲሆን፤ በግማሽ ዓመቱ 200 ኪሎ ግራም እንደሚመረት ይጠበቅ ነበር:: እስካሁን ያለው አፈጻጸም 36 ነጥብ 6 ኪሎ ግራም ነው። ይህ ትልቅ ክፍተት እንደሆነም ይገልፃሉ::

በ2014 በጀት ዓመት እስከ 400 ኪሎ ግራም የወርቅ ምርት የተገኘበት ሁኔታ እንደነበር አስታውሰው፣ አሁን የሚታዩት ብልሹ አሠራሮች ከተቀረፉና ትኩረት ተሰጥቶት በደንብ ከተሰራ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ምክትል ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል::

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በኢንዱስትሪ ማዕድንም በግራናይት፣ ዳሜንሽን ስቶን እና ካዮሊንን በማምረት ረገድ የተጀመሩ ሥራዎች አሉ፤ ካዮሊን 90 በመቶው ለሴራሚክ ፋብሪካ የሚፈለግ ማዕድን ነው:: ሆኖም ግን በአካባቢው ኢንዱስትሪው ስለሌለ አምራቾቹ ይህንን አፈር ጭነው፣ ረጅም ርቀት ተጉዘው ኢንዱስትሪው ወዳለበት ቦታ ማድረሱ አዋጭ አልሆነላቸውም። የማዕድኑ በዚህ ልክ መገኘት በክልሉ የሴራሚክ ፋብሪካዎች የሚከፈቱበትን እድሉ ያሰፋዋል:: በዚህ ማዕድን ፈቃድ የወሰደው አምራችም ፈቃዱን ይዞ ሌላ አማራጭ እየጠበቀ እንደሚገኝ ምክትል ዳይሬክተሩ አመላክተዋል::

> **ለሴራሚክ ማምረት ስራ ግብዓት የሚውሉ ካዮሊን፣ ግራናይት፣ እምነበረድ፣ የኖራ ድንጋይ እና የመሳሰሉት ማዕድናት በክልሉ በስፋት ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ማዕድናት ለማልማት አልሚዎች ማዕድኑን በጥናት በመለየት ወደ ምርት ፈቃድ ደረጃ እየተሸጋገሩ ይገኛሉ**

የግራናይትና የኖራ ድንጋይ ማዕድናትን ለማምረት የሚፈልጉ አካላት ፈቃድ ያገኙት በዚህ ዓመት በመሆኑ፤ በዚህ በኩል ያሉት ሥራዎች ገና በጅምር ላይ ናቸው። ብረትና ብረትነክ ማዕድናትንም በተመለከተ እስካሁን ምርመራውን ጨርሶ ወደ ምርት የገባ የለም::

በማዕድኑ ዘርፍ እየተሰሩ ያሉት ሥራዎች ተስፋ ሰጪ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የትኩረት አቅጣጫውን ተከትሎ እንደሚሰራ አስታውቀዋል:: ሀገር ውስጥ ያለውን ሀብት በመለየትና በማልማት ለኢኮኖሚ እድገት በገቢ ምንጭነት ወይም በግብዓትነት መጠቀም ምርጫ እንደሌለውም አስታውቀዋል::

## መፍትሔዎች

ከድንጋይ ከሰል ምርት ጥራት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በማዕድን ሚኒስቴር ኢንዱስትሪ ኢንሼቲቭ አማካኝነት ኢንዱስትሪዎች ምን አይነት የድንጋይ ከሰል ምርት ያስፈልጋቸዋል? ምን አይነት ምርትስ አለ? በሚለው ላይ ጥናት ማካሄድ መጀመሩን ምክትል ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል:: እሳቸው እንዳሉት፤ ጥናቱ ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን የድንጋይ ከሰል ካሎሪ መጠን ለመለየት የሚያስችል ነው:: አሁን በአብዛኛዎቹ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከስድስት ሺ በላይ ካሎሪ መጠን ያለው የድንጋይ ከሰል ነው የሚቀበሉት:: ከዚህ በታች ካሎሪ ያለውን የድንጋይ ከሰል አንቀበልም የሚሉበት ሁኔታ አለ:: የጨርቃጨርቅ፣ የቀለም እና የመሳሰሉት ፋብሪካዎች ደግሞ ከዚህ ዝቅ ያለ የካሎሪ መጠን ይጠቀማሉ:: ይህን ፍላጎት በመለየት አስተማማኝ የገበያ ትስስር ለመፍጠር እየተሰራ ነው::

እስከዚያ ግን በዳውሮ ዞን የተተከለው የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ /ፕሮሰሲንግ/ ማሽን በቀን አንድ ሺ500 ቶን የድንጋይ ከሰል ማጠብ ይችላል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ፋብሪካው በድንጋይ ከሰል ምርት ላይ ያለውን የጥራት ችግር ሊፈታ እንደሚችል ታምኖበት እየተሰራ እንደሆነ ይገልጻሉ:: ተጨማሪ የማጣሪያ ማሽን ለመትከል ፍላጎት ያላቸው ሌሎች አምራቶች መኖራቸውንም ጠቅሰው፤ አሁን ላይ እየታየ ያለው ጅምር ጥሩ እንደሆነ አመላክተዋል::

የወርቅ ማምረትን በተመለከተም ወርቅ በሚመረትበት ቤሮ ወረዳ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ መከፈቱን ጠቅሰው፣ አምራቾች የወርቅ ምርቱን ለባንኩ እንዲያስገቡ የሚደረግበት ሁኔታ መፈጠሩን አስታውቀዋል:: በዚህም በተወሰነ መልኩ ችግሩን ለመቅረፍ ተችሏል ብለዋል። አሁን እንደ ችግር የሚነሳው የኔትወርክና የመንገድ መሰረተ ልማት አለመኖር መሆኑን ጠቅሰው፣ የጸጥታ ችግር ሌላው የልማቱ ተግዳሮት መሆኑን አስታውቀዋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታትም እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል::

## ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

በማዕድን ዘርፍ በክልሉ ይህ ሁሉ ሀብት መኖሩ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች እንዳሉ ያመላክታሉ ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይ የተሻለ ጥናት ቢደረግ ሰፊ ሥራዎች መስራት እንደሚቻል አመላክተዋል:: የክልሉ የማእድን ሀብት ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት በመተካትና ምርቶቹን ወደውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት በኩል ተስፋ የተጣለበት መሆኑን ምክትል ዳይሬክተሩ ያስረዳሉ።

በቀጣይ በማዕድን ዘርፉ ላይ የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸው፣ በወርቅ ላይ ከባህላዊ ወርቅ አምራቾች በተጨማሪ ልዩ አነስተኛ ባለ ፈቃድ የሚባሉትም ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን አስታውቀዋል:: እነዚህ አምራቾች ማሽን ተጠቅመው የሚያመርቱት የወርቅ ምርት የተሻለ ውጤት ያመጣል ተብሎ እንደሚጠበቅም ነው ያመለከቱት::

ይህ ሁኔታ በድንጋይ ከሰል አምራቾች ዘንድም መነቃቃት እንዲፈጠር ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል:: የበጋ ወቅት ለማዕድን ሥራዎች ምቹ መሆኑን ጠቅሰው፣ አምራቾቹ በዚህ ወቅት በሙሉ አቅም ወደሥራ እንዲገቡ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የተሻለ አምርቶ የተሻለ ገቢ እንዲገኝ ለማድረግ ይሰራል ብለዋል::

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ደባና ፍርድ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ስንሻው የቤቱን በር ከፍቶ ሲገባ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት አለፍ ብሎ ነበር፡፡ ከሚሰራበት ቦታ በጊዜ ቢወጣም ወደ ቤቱ የሚገባው ግን አረፋፍዶ ነው። መብራት ሳያበራ ሄዶ አልጋው ላይ ዘፍ አለ። ጆሮዎቹን ወደ ውጪ ወረወራቸው ከዝምታ በቀር ምንም አላዳመጠም። ትናንትና የመንደሩ ሰዎች ሰፈሩን ይልቀቅልን ሲሉ የቀበሌው አስተዳዳሪ ጋር ሄደው ነበር። በእሱ ያልተማረረ አንድም ሰው ሰፈሩ ውስጥ የለም። ለምን ካላችሁኝ እንዲህ እላችኋለው . . . ስንሻው ውሸታም ነው . . . ከውሸቱ በላይ ብድር በመጠየቅ ተወዳዳሪ የለውም፡፡ በዚህ መንታ ድርጊቱ የሰፈሩ ሰው ጠላው፡፡ "ከሀገር ይውጣልን" ሲሉም አመጹበት። ከመንደሩ ሰው ለመሸሽ ሲልም አምሽቶ ወደ ቤት መግባትን ልማድ አደረገው፡፡

ስንሻው የሀጢያት ጠቢብ ነው . . . እውቀቱን ለእኩይ ነገር የተጠቀመ አንድ ሰው ቢኖር ስንሻው ብቻ ነው፡፡ ከአንድ ሰው የሆነ ነገር ከፈለገ መጀመሪያ ያን ሰው በማሞገስና በማድነቅ ነው የሚጀምረው፡፡ ሰፈሩ ውስጥ የተበደራቸውን ሰዎች ሁሉ በአድናቆትና በሙገሳ ጀምሮ ኪሳቸውን ያራቆታቸው ናቸው፡፡ እሱ ሲናገርና ቅዱስ ጳውሎስ ሲሰብክ አንድ ነው፡፡ አፉ የጅብ ጥላ ነው . . . አፍዝ፣ አደንግዝ፡፡ ብድር ወስዶ ከከለከላቸው የመንደሩ ሰዎች መካከል እማሆይ ምንትዋብ አንዷ ናቸው፡፡ ደጅ ሰላም ድረስ ሄዶ ነበር "ነገ እመልሳለሁ፤ አዛኝቷ ምስክር ትሁነኝ" ብሎ የተቀበላቸው፡፡ አንድም ቀን መልሶላቸው አያውቅም። እሳቸውም አንድም ቀን ከልክለውት አያውቁም፡፡ ተበድሮ ካስቀረባቸው ሰዎች መካከል እማማ ባንቺ ይርጉም አንዷ ናቸው። ሽሮና በርበሬ ወደሚሸጡበት የጉልት ገበያ ይሄድና "እናት አለሜ" ይላቸዋል ከአዳፋ ሻሻቸው ያመለጠ ነጭ ሽበታቸውን ወደ ማደሪያው እያጎረ፡፡ ከዛም አሳዛኝ አይኑን በእርጅና የሞጨሞጨ አይናቸው ላይ ያስለመልመዋል፡፡ ያኔ ወላድ ሆዳቸው ቦጭ ... ቦጭ ይላል፡፡

ለምን እንደሚመጣ እያወቁም "ምነው. . . ምን እግር ጣለህ ይሉታል . . .፡፡ እንደ ሻሻቸው ያደፈ አሮጌ ጃንጥላቸውን ከጸሀዩ ሊከልሉት ወደ እሱ እያዩ፡፡

"ድሀ ምን ማረፊያ አለው . . . ይሄው እባክናለሁ።"

"አይዞህ! ሁሉም ያልፋል፤ መበርታት ነው" ይሉታል እውነት፣ እምነት፣ ደግነት በሚያውቁ አዛውንት አይናቸው እያስተዋሉት፡፡

‹እርሶ እኮ ገነቴ ኖት፤ እርሶ ባይኖሩ ኖሮ ውሻም በጨው አይቀምሰኝ ነበር፡፡ ሳይደግስ አይጣላ፣ እርሶን ጥሎልኛል› ሲል ወደ ሰማይ ይመለከታል። ቀጥሎም ‹እንዳው . . . ነገ የምመልሰው ጥቂት ገንዘብ ካሎት› ይላቸዋል ፊቱን፣ ነፍሱን አሳዝኖ፣ ባዘነ . . . በተራቆተ ባዶ ሰውነት፡፡

መቀነታቸውን ፈትተው "እንካ፣ ይቺ ናት ያለችኝ . . ዛሬ ምንም አልሸጥኩም፡፡" ይሉታል ከእሱ ባልተናነሰ እዝን ውስጥ ወድቀው፡፡ በመጣ ቁጥር እንደሰጡት ነው፡፡ ካላቸው ከመቀነታቸው ላይ ፈትተው፣ ከሌላቸው ደግሞ አጠገባቸው ከምትሸጠው ወጣት ሴት ላይ ተበድረው ይሰጡታል፡፡ እማማ ባንቺ ይርጉ ነገን አያውቁትም . . .፤ እርጅና ነው መሰለኝ ነገ መቼ እንደሆነ ዘንግተውታል፡፡ ስንሻውም ይሄን ደካማ ጎናቸውን ሰበብ አድርጎ ሁሌ ማታ ማታ "ነገ እመልሳለሁ" እያለ ገንዘብ ይወስድባቸዋል። እሳቸው ነገን አያውቁትም . . . አጠገባቸው መጥቶ ገንዘብ ሲላቸው ትናንት የወሰደውን መልሶ የሚጠይቃቸው ነው የሚመስላቸው፡፡ ብዙ ቀን "ነገ እመልሳለሁ" ብሎ የሸጡትን ሁሉ ወስዶባቸው ያውቃል፡፡ ብዙ ቀን ነገን ስለማያውቁ በእርጅናቸው ተጫውቶ ያውቃል። ብዙ ቀን በእውነታቸው ላይ ተረማምዶ ዋሽቷቸው ያውቃል፡፡ እማማ ባንቺ ይርጉ ቀን ሙሉ የሸጡትን ለእሱ አበድረው ቤታቸው ባዶ እጃቸውን ገብተው ያውቃሉ፡፡ "ነገ እመልሳለሁ፤ አበድሩኝ" ብለው ጎረቤት ሄደው ያውቃሉ፡፡

አሁንም ሰጡት . . . በእውነት፣ በእምነት፡፡ ሰላላ እጃቸውን ወደ መቀነታቸው ሲሰዱ የተረፈ አንዳችም ገንዘብ አልነበራቸውም፡፡ ከመቀነታቸው ላይ ቀና ሲሉ ስንሻውን ካጠገባቸው አጡት፡፡ በርቀት እሱን የሚመስል ሰው አዩ፡፡ በምን ፍጥነት ከዚህ እስከዛ እንደሄደ አላውቅ አሉ፡፡ ሁሌ ሳያዩት ነው የሚሄደው፣ ሁሌ እንዲህ እንደ አሁኑ ገንዘብ ሊሰጡት የፈቱትን መቀነታቸውን ለማጥበቅ ጎንበስ ባሉበት ነው ትቷቸው የሚሄደው፡፡ ሲመጣ እንጂ ሲሄድ አይተውት አያውቁም፡፡ ሲመጣ፣ አጠገባቸው ሲቆም መላዕክ ሆኖ ነው፣ ሲሄድ ግን እንደ ሰይጣን ነው .. ሳያዩት፣ ሳይሰሙት ብን ብሎ። ደግሞ አንድም ቀን አመስግኗቸው አያውቅም፡፡

የስንሻውን እግር ተከትሎ አንድ ችግረኛ ‹ስለ ለማርያም . . .› ሲል ተጠጋቸው፡፡ ምን ይስጡት? መቀነታቸው ባዶ ነው፡፡ ሻሼ ላይ ካለ ብለው አዳፋ ሻሻቸውን ፈተሹ፤ ለምስኪኑ የሚሆን አንዳች አላገኙም። ወደ ድሀው አዩ . . . እጁን ዘርግቶ እየጠበቃቸው ነው። ከበርበሬው አራት ማንኪያ፣ ከሽሮው አራት ማንኪያ አድርገው በፌስታል ጠቅልለው እንካ አሉት፡፡

"ይቅርታ እናቴ! የምገዛበት ምንም ፍራንክ የለኝም . . . ልለምን ነው ፊትዎ የቆምኩት . . . በልገሳ የሚሰጡኝ ከሆነ ልቀበሎት" አፐለ . . .፤ ስጦታ መሆኑን ባለማመን፡፡

‹እጄ ላይ የምሰጥህ ሳጣ ነው ሽሮና በርበሬ የሰጠሁህ። የሚያስከፋህ ከሆነ ትንሽ ቆይተህ ናና በገንዘብ እቀይርልሀለው› አሉት፡፡

እጃቸውን ስሞ ተቀበላቸው፡፡ ከእናት አንደበት ያን ያክል ትህትና ሰምቶ አያውቅም፡፡ በዘመኑ ለምኖ ካገኘው ሁሉ ያን እለት በለጠበት። በዘመኑ ከተቀበለው ሁሉ በዛን ቀን ከነዛ አሮጊት የተቀበለው ላቀበት፡፡ ሰው ለካ እያለው ከሚሰጥ ከሌለው ላይ ቢሰጥ ይበልጥ ኖሯል...። ብዙዎች ካላቸው ላይ ነው የሚሰጡት ካላቸው ላይ ካልሆነ ከሌላቸው ላይ ተቀብሎ አያውቅም፡፡ ያላቸው ካልሆኑ የሌላቸው ሰጥተውት አያውቁም። ሰው ገንዘብ ኪሱ ከሌለ የሚሰጠው ያለ አይመስለውም። እኛ ኪሳችንን ብቻ ስለምንፈትሽ እንጂ ልባችንን መፈተሽ ብንችል የምንሰጠው ብዙ ነገር ነበር፡፡ እኚህ እናትም ያስተማሩት ይሄን ነው፡፡ መቀነታቸው ሲነጥፍ ወደ አዳፋ ሻሻቸው ማተሩ። በዛም አንዳች ሲያጡ እንሆ ካላቸው ላይ አካፈሉት። እሳቸው ለእሱ መስጠት ከሰሰቱ ባለጸጋና ከበርቴ መሀል ከመቀነቷ ላይ ፈትታ ያላትን አንድ ሳንቲም ለጌታ እንደሰጠችው ድሀ ሴት ናቸው፡፡

እማማ ባንቺ ይርጉ "ማርያም" ተብለው አጥተው አያውቁም፡፡ ደሀ ፊታቸው ቆሞ "የለኝም" ብለው አያውቁም፡፡ መስጠት የማይሰለቸው እጅ፣ ማዘን የማይሰለቸው ልብ፣ ጸጋና በረከት የተሞላ ሴትነት። ሁሉን የሚያውቁት ቤት ሲደርሱ ነው ...። ሌማቱ ባዶ እንደሆነ፣ ቦሀቃው ሊጥ እንደሌለው የሚያውቁት ማታ ነው . . ቤት ሲደርሱ . . . ግን ሁሉ እንዳለው ባለጸጋ ናቸው፡፡

..........

ያን ቀን ስንሻው ወደ ቤቱ አልተመለሰም . . . ከእማማ ባንቺ ይርጉ እንደ ተለየ ከየት መጣ የማይባል መኪና አግኝቶ ገደለው፡፡ ደባና ፍርድ፡፡

ጠዋት ጉልት ሲደርሱ አጠገባቸው ካለችው ወጣት በመኪና አደጋ ህይወቱ ማለፉን ነገረቻቸው። ግራ የሚያጋባ ወሬ ሰሙ . . . ከእርሶ ላይ እየመጣ ገንዘብ የሚበደረው፤ ተበድሮ የሄደው።

"ማነው እርሱ . . .?"

# ዓለም አቀፍ



## አሜሪካ የሀውቲን የጸረ-መርከብ ሚሳይል መምታቷን አስታወቀች

አሜሪካ የሀውቲን የጸረ-መርከብ ሚሳይል መምታቷን አስታወቀች። የአሜሪካ ጦር ሰኞ ዕለት በየመን በሀውቲ ይዞታ ስር ባለ ቦታ በጸረ-መርከብ ሚሳይል ላይ አዲስ ጥቃት ፈጽማለች።በቀይ ባህር ስትንቀሳቀስ የነበረች የግሪክ መርከብ ጥቃት እንደደረሰባት ሮይተርስ ዘግቧል።

በኢራን ይደገፋል የሚባለው የሀውቲ ታጣቂ ቡድን ከባለፈው ህዳር ወር ጀምሮ በቀይ ባህር በሚንቀሳቀሱ መርከቦች ላይ የሚያደርሰው ጥቃት በብዙ ኩባንያዎች ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። ሀውቲዎች በቀይ ባህር ላይ ጥቃት የሚሰነዝሩት ከእስራኤል ጋር እየተዋጋ ላለው ሀማስ አጋርነት ለማሳየት እንደሆነ መግለጻቸው ይታወሳል።

በቀይ ባህር የሚንቀሳቀሱ መርከቦችን ደህንነት አስጠብቃለሁ የምትለው አሜሪካ፣ በርካታ ሀገራትን ያካተተ ግብረ ኃይል አቋቁማ ወደ ስራ ገብታለች።በቅርቡ አሜሪካ እና ዩኬ በየመን ግዛት ውስጥ በሀውቲ ቡድን ይዞታ ላይ ጥቃት አድርሰዋል፤ የሀውቲ ታጣቂዎችም ለደረሰው ጥቃት ምላሽ እንደሚሰጡ መዛታቸው የሚታወስ ነው።

ሀውቲዎች ገንዘብ እና የጦር መሳሪያ እንዳይደርሳቸው፣ የአሜሪካው ፕሬዚንት ጆ ባይደን አስተዳደር በድጋሚ የሽብር ቡድን ዝርዝር ውስጥ ሊከታቸው እንደሚችል ሮይተርስ ዘግቧል።እስራኤል እና ሀማስ ግጭት መቀስቀሱን ተከትሎ የተከሰተው የቀይ ባህር ውጥረት እየጨመረ መጥቷል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

## ሕግ የማያከብሩ የጣሊያን ማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ቅጣት ሊጣልባቸው ነው

የጣሊያን ማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ይዘታቸውን በሚለጥፉበት ጊዜ ልክ እንደ መደበኛ መገናኛ ብዙኃን በተመሳሳይ ህጎች ሊገዙ ይችላሉ ተብሏል። የተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንቅስቃሴ በጣሊያን ኮሙዩኒኬሽን ባለስልጣን ቁጥጥር ስር ሊገባ ነው ሲል ተቋሙ ተናግሯል።

ደንቦቹ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ተከታዮች ባሏቸው የይዘት ፈጣሪዎች ላይ ቀድመው ተፈጻሚ ይሆናሉ። የባለስልጣኑ ኃላፊ ጂያኮሞ ላሶሬላ "የተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንደፈለጉ መሆን አብቅቷል" ብለዋል።"እኛ ከትላልቆቹ ነው የምንጀምረው። ነገር ግን ሌሎች ተፅዕኖ ፈጣሪዎችም መላመድ አለባቸው" ሲሉ ለላ ሪፐብሊካ ጋዜጣ ተናግረዋል።



ታዋቂ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ማስታወቂያ እየሠሩ እንደሆነ በግልጽ ካላስቀመጡ ወይም የንግድ ግንኙነታቸውን ይፋ ካላደረጉ ከፍተኛ ቅጣት ይጠብቃቸዋል።መመሪያዎቹ ህጻናትን ለመጠበቅ ያለሙ ሲሆኑ በአዲሱ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከተቋማት እና ከንግድ ጥቅማቸው ጋር ያላቸውን ትብብር በትክክል ማስተዋወቅ ያልቻሉ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች 250 ሺህ ዩሮ የሚደርስ ቅጣትን ጨምሮ እስከ ከባድ ቅጣቶች ይጠብቃቸዋል።

ባለስልጣኑ በመግለጫው እንዳስታወቀው እርምጃዎቹ "የንግድ ግንኙነቶችን፣ የሰዎችን መሠረታዊ መብቶችን፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን እና የስፖርት እሴቶችን መጠበቅን ይመለከታሉ" ብሏል። ምርት በማስቀመጥ የሚደረግን ማስታወቂያ በተመለከተ ደግሞ "ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ስለማስታወቂያው ይዘት ማስጠንቀቂያ ማስገባት አለባቸው" ብሏል መግለጫው።

ብዙዎች የባለስልጣኑን ውሳኔ ከጣሊያን ከፍተኛ ተጽእኖ ፈጣሪ ቺያራ ፌራግኒ ጋር የተገናኘ እንደሆነ አድርገው ቢመለከቱትም ላሶሬላ ግን ውድቅ አድርገውታል። ባለፈው ታህሳስ በኢንስታግራም ላይ ወደ 30 ሚሊዮን የሚጠጉ ተከታዮች ያሏት ፌራግኒ "ከዲዛይነር" ሮዝ የገና ኬክ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ በቱሪን የሚገኘውን የሕጻናት ሆስፒታል ይደግፋል በማለቷ 1.075 ሚሊዮን ዩሮ ተቀጥታለች። የኬኩ አዘጋጅ ኬኩ ለሽያጭ ከመዋሉ ከወራት በፊት ገንዘቡን ለሆስፒታሉ ሰጥቷል።

በኋላም ለተከታዮቿ ባሰራጨችው መግለጫ "የንግድ እንቅስቃሴን ከበጎ አድራጎት ጋር በማያያዝ...በቅን ልቦና የተሠራ ስህተት ነው" ስትል ተናግራለች። የጣሊያን ፖሊስ በበኩሉ ባለፈው ሳምንት ፌራግኒ በገና ኬክ ወይም በፓንዶሮ ጉዳይ ላይ በማጭበርበር ወንጀል ምርመራ እንደሚደረግባት አስታውቋል።

ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ላይ ጥብቅ ህጎች የሚያሳርፈው አሠራር ባለፈው ዓመት ነው በሌሎች የአውሮፓ ሀገራት የወጣው። ባለፈው ሰኔ ፈረንሳይ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች አዲስ የማስተዋወቂያ ደንቦችን ጥሰው ከተገኙ የእስራት ጊዜ ሊጠብቃቸው እንደሚችል የሚገልጽ ህግ አውጥታለች። ይህም በአውሮፓ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የአውሮፓ ኮሚሽን በበኩሉ የዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች "ፍትሃዊ የንግድ ልምዶችን መከተል እና ተከታዮቻቸው ግልጽ እና አስተማማኝ መረጃ የማግኘት መብት እንዳላቸው" በመግለጽ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎችን እና የተፅዕኖ ፈጣሪዎችን መከታተሉን እንደሚያጠናክር አስታውቋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ዓርብ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ውድድሮች በሚካሄድበት የውድድር ዓመት ውጤታማነትን ለማስጠበቅ

ብርሃን ፈይሳ

ያለፈው የውድድር ዓመት በኢትዮጵያ አትሌቲክስ መልካም ውጤት የተመዘገበበት ሆኖ ነበር ያለፈው። በዚህ ዓመት ደግሞ ኦሊምፒክን ጨምሮ በርካታ ታላላቅ ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚከናወኑበት ነው። በመሆኑም ለዓለም አቀፎቹ ውድድሮች እንደ ማጣሪያ የሚሆኑ የሃገር ውስጥ ቻምፒዮናዎች በጊዜ መርሃ ግብሩ መሰረት በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ካለፈው ዓመት በርካታ ተሞክሮዎችን የቀሰመው ፌዴሬሽኑ በዓመቱ ስፖርቱን በምን መልክ እንደሚመራ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ከነበረው ውጤት የተሻለ ለማስመዝገብ የያዘው እቅድ ይህን ይመስላል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዮሃንስ እንግዳ፤ የተያዘው የውድድር ዓመት በአትሌቲክስ ስፖርት በአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ውድድሮች "የተጨናነቀ ሊባል የሚችል መሆኑን ይጠቁማሉ። በአህጉር አቀፍ ደረጃ በቅርቡ የሚከናወነውን ሃገር አቋራጭ ውድድር ጨምሮ የአፍሪካ ቻምፒዮና እንዲሁም የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች ይከናወናሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና፣ የሃገር አቋራጭ፣ የዓለም ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮና፤ እንዲሁም የፓሪሱ ኦሊምፒክ ይካሄዳል። በመሆኑም ኢትዮጵያ ለምትወከልባቸው እነዚህ ውድድሮች ከ10 ያላነሱ የሃገር ውስጥ ቻምፒዮናዎች ይከናወናሉ፡፡ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ የነበራትን ውጤት



የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዮሃንስ እንግዳ፤

አስጠብቃ እንድትቀጥልም ጥረት ይደረጋል፡፡

አጠቃላይ ለእነዚህ ውድድሮች የሚሆነውን ዝግጅት አስመልክቶም ፌዴሬሽኑ ከወዲሁ ስራዎችን የጀመረ ሲሆን፤ ለአብነት ያህል ለዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና የመጀመሪያ ዙር አትሌቶች ምርጫ ተደርጓል፡፡ በቀጣይ ጊዜያትም በቤት ውስጥ የቱር ውድድሮች በሚመዘገበው ውጤት መሰረት የመጨረሻው የአትሌቶች ምርጫ በማድረግ ከ800 እስከ 3ሺህ ሜትር መሰናክል ባሉት ርቀቶች ዝግጅት የሚደረግ ይሆናል፡፡ የመጨረሻው ምርጫ እስኪታወቅም አትሌቶች ለሚያደርጉት የግል ውድድር ፌዴሬሽኑ ለልምምድ የሚረዳቸውን የማዘውተሪያ ስፍራ በማመቻቸት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። ይህ ሁኔታ በሌሎች ውድድሮች ላይም በተመሳሳይ ይቀጥላል፡፡

የዓመቱ ትልቁ ውድድር የፓሪሱ ኦሊምፒክ እንደመሆኑ ኢትዮጵያ በምትካፈልባቸው የአትሌቲክስ ርቀቶች አትሌቶችን አስቀድሞ መለየት ተችሏል፡፡ እስከ መጪው ነሐሴ ወር 2016 ዓ.ም በሚኖረው ሰፊ ጊዜም ይኸው እየተጣራ የሚቀጥል ሲሆን፤ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችም በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ ይህ ውድድር የሚመራው በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እንደመሆኑ ከሁለቱ ተቋማት የተወጣጡ ባለሙያዎችን ያቀፈ የቴክኒክ ኮሚቴ ተዋቅሮ ካለፉት ኦሊምፒኮች የተሻለ ውጤት እንዲገኝ ከወዲሁ እየተሰራ ነው፡፡ ሁለቱ አካላት በመግባባትና መናበብም ለጥሩ ተሳትፎና ዝግጅት እየተጉ እንደሚገኙም ነው ኃላፊው ያብራሩት፡፡

ኢትዮጵያ በመላው ዓለም ስሟ በመልካም እንዲነሳ ካደረጉ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው አትሌቲክስ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ይሁንና በብርቱ አትሌቶቿ የተገነባው ይህ በጎ ገጽታ እንዲወይብ የሚያደርጉ ክስተቶች በዚሁ ስፖርት መስተዋሉ አልቀረም፡፡ የስፖርቱን ዓለም እያመሰ የሚገኘውና እንደ ሩሲያ ያሉ ሃገራትን ከየትኛውም ውድድር ያሳገደ እነ ኬንያን ደግሞ በዓይነ ቁራኛ እንዲታዩ ያደረጋቸው የስፖርት አበረታች ቅመሞች ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ታዲያ ይኸው የስፖርቱ ጥቁር ገጽ በኢትዮጵያም መታየት ከጀመረ ዋል አደር ያለ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ኢትዮጵያን እስከመወከል በደረሱ ትልልቅ አትሌቶች ጭምር ተጠቃሚነቱ እየሰፋ መጥቷል። ፌዴሬሽኑም ባለፈውና በተያዘው የውድድር ዓመት አስከፊ ወደሆነ ደረጃ እየተሸጋገረ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የአበረታች ቅመም ተጠቃሚነት አሳሳቢ መሆኑን ያነሱት ኃላፊው፤ ፌዴሬሽኑ በጉዳዩ ላይ የማያወላዳ አቋም እንዳለውና የትኛውም አትሌት በዚህ ድርጊት መሳተፉ ከተደረሰበት እርምጃ እንደሚወሰድበት ያረጋግጣሉ፡፡

ፌዴሬሽኑ አትሌቶችን የሚከታተሉ ባለሙያዎች ያሉት እንደመሆኑ ግንዛቤ በመፍጠር የድርሻውን እየተወጣ ነው፡፡ ነገር ግን የአበረታች ቅመም ተጠቃሚ የሆኑት አትሌቶች ካሉበት ደረጃ አንጻር ግንዛቤ የላቸውም ለማለት አዳጋች ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው የቅመሞቹን ምንነት አውቆ በአንድ ውድድር ላይ ብቻ በከፍተኛ መጠን የመጠቀም ዝንባሌ መኖሩ ነው። ፌዴሬሽኑ በዚህ ላይ ጠንካራ አቋም ያለው ሲሆን፣ መሰል ተግባር ላይ የሚሳተፉ አትሌቶች ላይም አስተማሪ የሆነ ቅጣት ይወስድባቸዋል፡፡ በዚህም ላይ ፌዴሬሽኑ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጠንካራ ስራ እያከናወነ እንደሆነም ነው ኃላፊው ያስገነዘቡት፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
Ministry of Labor and Skills

## ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም


# ተቋማትን በቀጣና የመክፈል እና በሥልጠና መስኮች የመለየት ጥቅም

ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከኢንዱስትሪዎች ጋር ቁልፍ ትስስር እንዲፈጥሩ ማድረግ ለነገ የማይባል ጉዳይ መሆን እንዳለበት ይገለፃል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የመጀመሪያው ምክንያት የቴክኒክና ሙያ ቀዳሚ ተገልጋዮቻቸው ኢንደስትሪዎች መሆናቸው ነው። የሥልጠና ተቋማት ሥርዓተ ስልጠናቸውን የሚቀርጹት ኢንዱስትሪዎችን በማሳተፍ ለገበያው የሚመጥን ሙያ በሚያወጡበት መንገድ ነው። ያሰለጠኗቸውም ብቁ ሙያተኞች የሚቀላቀሉት የሥራ መስክ በዚሁ የተቃኘ ነው። የሥልጠና ተቋማቱ ሠልጣኞችን የሚያወጡትም ለእነዚህ ኢንዱስትሪዎች እንዲመጥኑ፣ ተወዳድረው እንዲያሸንፉና ብቁ እንዲሆኑ አድርገው ነው፡፡

ሌላኛው ምክንያት የቴክኒክና ሙያ ሰፊ ሀብት የሚጠይቅ ዘርፍ (capital intensive) በመሆኑ ነው። አንድ የሥልጠና ተቋም ሁሉም የሥልጠና መስኮች የሚጠይቁትን ቁሳቁስ ያሟላል ብሎ መነሳት በተለይም እንደኛ ሀገር ኢኮኖሚያቸው ገና ባላደገ ሀገራት አዳጋች ነው። ስለሆነም ኢንዱስትሪዎች በገነቧቸው ፋብሪካዎች ላይ የተግባር ሥልጠናን መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ትስስር መፍጠር የግድ የሚል ተግባር ነው፡፡

ለዚህ ጽሁፍ የተመረጠው ሦስተኛው ምክንያት ቴክኖሎጂ ተለዋዋጭ በመሆኑ ነው። ቴክኖሎጂዎች በተለዋወጡ ቁጥር የሥልጠና ተቋማት ቴክኖሎጂዎቻቸውን መቀያየር አዳጋች ይሆንባቸዋል። ፋብሪካዎች ግን ይህ እድል አላቸው። በአጠቃላይ ከላይ በጠቀስናቸውና በሌሎችም ምክንያቶች የሥልጠና ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች ቁልፍ ትስስር አላቸው።

ኢንዱስትሪዎች በአንድ አካባቢ የሚመሠረቱት በአካባቢው የሚገኘውን ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብት መነሻ አድርጎ ነው። ቁሳዊ ሀብቱ ተፈጥሯዊ ቢሆንም ተፈጥሮውን የሚያለማ የሠለጠነ የሠው ኃይል ይፈልጋል። ይህ የሰው




ኃይል ደግሞ የሚገኘው ከቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ነው። ለዚህ ነው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትን በአካባቢያቸው ያለውን ሀብት መሠረት በማድረግ በዞን መከፋፈል ያስፈለገው።

በሀገራችን የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ የራሱ ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች ከተዘጋጁበት ጊዜ አንስቶ ተቋማትን በቀጠና መከፋፈል (#Zoning) እና የሥልጠና መስኮች ልየታ (#Differentiation) የሚሉ ጽንሰ-ሀሳቦች ተደጋግመው ሲነሱ እናስተውላለን፡፡

### የልየታው ምንነት

በሀገራችን የቴክኒክና ሙያ ሠልጣኞች ተመርቀው ሲወጡ የሚቀላቀሉበትን የኢንደስትሪ ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ አይደሉም እየተባሉ ተደጋጋሚ ወቀሳዎች ይሰነዘራሉ፤ አንድም ጥራት ያለው ሥልጠና አግኝተው አይወጡም አሊያም ሥልጠናው ጥራት ቢኖረውም ከኢንዱስትሪው ፍላጎት ጋር ያለመጣጣም ችግር አለበት። በዚህ ምክንያት የገበያ አለመጣጣም ይከሰታል የሚሉ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡

ተቋማት የሚሰጧቸው ሥልጠናዎች አካባቢያዊ አቅምን ያገናዘቡ አለመሆናቸው፤ የአካባቢያቸው ኢንዱስትሪ የሚፈልገውን ሥልጠና ለይተው አለመስጠታቸው እንደተጨማሪ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡ በሌላ በኩል በሀገራችን ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰጡት ሥልጠናዎች በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆኑ በተመሳሳይ መስኮች ሰፊ ቁጥር ያላቸው ተመራቂዎች ይወጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሥራ አጥ ቁጥር መጨመር አንዱ ምክንያት ነው፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እንደሀገር የተለያዩ የመፍትሔ አማራጮች ተሞክረዋል፡፡ ነገር ግን የችግሩን ስፋት ያህል ውጤት አላመጡም፡፡ ከእነዚህ ሙከራዎች ትምህርት ተወስዶ በቀጠና መከፋፈል (#Zoning) እና የሥልጠና መስኮች ልየታ (#Differentiation) እንደ አንድ የመፍትሔ አቅጣጫ ተወስዷል፡፡

በቀጠና መከፋፈልና የሥልጠና መስኮች ልየታ ኢትዮጵያን በአካባቢያዊ ሀብቶች (ግብርና፣ ኢንደስትሪ፣ ማዕድን፣ ...) በመለየት በኢኮኖሚ ኮሪደሮች መክፈል ማለት ነው፡፡ በእያንዳንዱ አካባቢ ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት በዚያ አካባቢ ባለው የሀብት ክምችት ይወሰናል።

ዓለምአቀፍ ልምዶችን ማየት እንደተቻለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት የሚዋቀሩት የኢንዱስትሪ ስብጥርን ታሳቢ አድርገው ነው፡፡ ኢንደስትሪው ደግሞ ቀድሞም የተዋቀረው አካባቢያዊ ሀብትን መሰረት አድርጎ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለሆነም ያንን ሀብት ሊያሳድግ የሚችል ሥልጠና መስጠት እንዲቻል በኢኮኖሚ ኮሪደሮች የመከፋፈል ሥራ (#Zoning) ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ያለውን ሀብት መሰረት አድርጎ የተፈጠረውን ቀጣና ወይም የኢኮኖሚ ኮሪደር መሰረት አድርጎ በሥልጠና ተቋማት የትምህርት ክፍሎችን የማደራጀት ሥራም የሚሠራ ይሆናል፡፡

ለአብነትም በቤኒሻንጉል ክልል ወደ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ አካባቢ የሚገኙ ተቋማት እንደ አሳ ልማት፣ መስኖ ልማት ያሉ ዘርፎች ላይ እንዲያሠለጥኑ፤ የማዕድን ሀብት የተከማቸባቸው አካባቢዎች ደግሞ በማዕድን ልማት ላይ እንዲያሠለጥኑ ማድረግ ማለት ነው፡፡

ተቋማቱ የአካባቢያቸውንና የማህረሰባቸውን ፍላጎት ያማከለ ሥልጠና እንዲሰጡና ሠልጣኞች ተግባራዊ ልምምድ ለማድረግ በቅርበት ኢንዱስትሪዎችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡ ቀደም ብለው የተለዩት የሥልጠና ጥራትና አግባብነት ችግሮች ከመፍታትም አንፃር የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል ተብሎ እምነት ተጥሎበታል፡፡